# በቀድሞ ዘመናት ከ፲፰፻፹፱* ዓ. ም. በፊት ውጭ አገር የተማሩ ኢትዮጵያውያኖች ታሪክ[1]

ዓለሜ እሸቴ

## በኢጣሊያን በቫቲካን የነበሩ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ፤

ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች በቀድሞ ዘመን ለትምህርት የሚሄዱት ብዙውን ጊዜ ወደ አውሮጳ ሲሆን ፤ በተለይም ደግሞ በቅድሚያና በብዛት የሚገኙት በጣሊያን አገር ውስጥ በቫቲካን ነበር ።

እንደሚታወቀው ፤ ኢትዮጵያውያን ቢያንስ ቢያንስ ከ፲፫ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም እየሄዱ የኢየሱስ ክርስቶስን መቃብር ይጎበኙ ነበር። በኢትዮጵያም ስም የተዘጋጀ ገዳም በኢየሩሳሌም ስለነበር ፤ ኢትዮጵያውያን መንፈሳውያን ሁሉ የሚያርፉት በዚሁ ነበር ። ኢየሩሳሌምም በሚቆዩበት ጊዜ ፤ በካቶሊካውያን ቀሳውስት ማበረታታት የተነሣም ሆነ ወይም በገዛ ፈቃዳቸው የቅዱስ ጴጥሮስን መቃብር ለማየትና የዚህንም ቅዱስ ተከታዮች ዋና መቀመጫ የሆነውን ሮምንና ቫቲካንን አልፎ አልፎ ሳይጎበኙ አይመለሱም ነበር ። በተለይም ደግሞ ግራኝ የክርስቲያንን ሃይማኖት ከኢትዮጵያ አጠፋለሁ ብሎ በተነሣ ጊዜና ከዚያም በተከታታይ በ፲፮ኛውና በ፲፯ኛው ክፍለ ዘመን የፖርቱጋል ሚሲዮናውያን የካቶሊክን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ከአስተዋወቁ በኋላ ፤ ወደ ቫቲካን የሚሄዱት መንፈሳውያን ኢትዮጵያውያን ቁጥር እየበዛ ሄዷል ።

ይህም ስለሆነ በቫቲካን ውስጥ ለኢትዮጵያውያን ጎብኝዎች ማረፊያ ቤት አስፈላጊ በመሆኑ ፤ በዚሁ ቅጥር ግቢ

* ሁሉም ዓመታት በተለይ ካልተገለጸ በስተቀር በዚህ ጥናት የተሰጡት እ. ኤ. አ. ነው ።

1. ይህ ጥናት "Foreign–educated Ethiopian: 1800–1889" ከተባለው በመዘጋጀት ላይ ከሚገኘው መጽሐፍ የተውጣጣ ነው ።

ከቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተያይዞ «ሳንቶ ስቴፋኖ ዴይ ሞሪ» ወይም «ሰንቶ ስቴፋኖ ዴሊ ኢንዲያኒ» የተባለው ተቋቋመ ። ይህም ገዳም ከብዙ ጊዜ በኋላ «ሳንቶ ስቴፋኖ ዴሊ አቤሲኒ» ተብሎ መጠራት ጀመረ ። በዚህም ገዳም የሚያርፉት አንዳንዶች ኢትዮጵያውያን በዚያ የሚቆዩበትን ጊዜ ስላራዘሙት ፤ ከጊዜ በኋላ ገዳሙ የኢትዮጵያ ጥናት ድርጅት ሆኖ አውሮጳውያን ከዚያ እየመጡ ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች ፤ ታሪክና ይህንንም የመሳሰለውን ሁሉ ይማሩ ጀመር ። ከነዚህም የመጀመሪያውና ከሁሉም ቀድሞ የሚታወቀው ጀርመናዊው ዮሐንስ ፓትከን በ፲፭፻፲፫ ዓ.ም. በሳንቶ ስቴፋኖ ከኢትዮጵያውያን መምህራን የግዕዝ ቋንቋ መማሩን አስታውቋል ። በመጀመሪያም ከታወቁት የዚህ ገዳም ኢትዮጵያውያን መምህራን አንዱ አባ ተስፋ ጽዮን ነበሩ ፤ እርሳቸውም ቫቲካን የመጡት በ፲፭፻፴፰ ዓ.ም. ነበር ። ከዚህም ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በአውሮጳ መታተም ጀመሩ ። አውሮጳውያን ወደዚሁ ገዳም መምጣት ቀጥለው ፤ በዚሁ መሠረት እጅግ የታወቀው ጀርመናዊ ኢዮብ ሉዶልፍስ በ፲፮፻፵፰ በዚሁ ስለ ኢትዮጵያ ባህል ታሪክና ቋንቋ ተምሮ ታላቅ ዋጋ ያለው ተብሎ የሚገመተውን የኢትዮጵያ ታሪክ ጽፏል ። እሱንም ከሚረዱት ኢትዮጵያውያን ዋነኛው የታወቁት አባ ጐርጐርዮስ ነበሩ።

እንደ አባ ተስፋ ጽዮን ያሉት በሳንቶ ስቴፋኖ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መምህራን ከጊዜያቸው ከፍለው እነሱ ደግሞ በበኩላቸው ስለአውሮጳውያን ታሪክ ፤ በተለይም የላቲን ቋንቋ ጥናት ያደርጉ ነበር ። የሆነ ሆኖ ከላይ እንደ ጠቀስነው የካቶሊክ ሚሲዮን በኢትዮጵያ ከተቋቋመ ወዲህ የሚስዮናውያኑ ታላቁ ምኞት የኢትዮጵያውያንን ካቶሊኮች ቁጥር ማብዛት ስለነበርና ለዚህም መልካም መሣሪያ ነው ብለው ያመኑበት ኢትዮጵያውያን የሆኑ የካቶሊክ ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ማዘጋጀት ስለነበር በሳንቶ ስቴፋኖስ ገዳም የካቶሊክን ሃይማኖት ከተቀበሉት መንፈሳውያን መሃል ሆነ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ እያሉ የካቶሊክን ሃይማኖት ከተቀበሉት መሃል ሮም «ኮሌጅዮ ኡርባኖ ዲ ፕሮፓጋንዳ ፊዴ» ተብሎ ወደሚጠራው የቀድሞ ዘመን ኮሌጅ እየላኩ ስለሃይማኖትና ስለ ፍልስፍና ያስተምርዋቸው ነበር። በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ፤ ኢዮብ ሉዶልፉስም እንደጻፈው ፤ በዚህ ኮሌጅ ሰባት ኢትዮጵያውያን ይገኙ ነበር ።

በቀድሞ ጊዜ በ «ኮሌጅዎ ዲ ፕሮፓጋንዳ ፊዴ» ከተማሩት ተማሪዎች በጣም የታወቀው ጦብያ ገብረ እግዚአብሔር የተባለው ነው ። ጦብያ ፤ ከአንድ ገብረ ክርስቶስ ከሚባል ጓደኛው ጋር ፤ ከኢትዮጵያ ተነሥቶ በኢየሩሳሌም አድርጎ ሮም የደረሰው በ፲፯፻፳፪ ዓ. ም. ነበር ። ከዚያም በቫቲካን ውስጥ ሳንቶ ስቴፋኖስ ገዳም እንዲያርፍ ተደርጐ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሦስት ዓመት እንደቆየ ሮም የሚገኙት የፕሮፓጋንዳ ፊዴ የታሪክ መዝገቦች ያረጋግጣሉ ። ከዚያም የካቶሊክን ሃይማኖት ተቀብሎ ፤ ለኢትዮጵያውያን የሚሆን የካቶሊክ እምነት ትምህርት ከላቲን ወደ ግዕዝ ተርጉሟል ። በመጨረሻም በ፲፯፻፳፰ ዓ.ም. ጦብያ ለኢትዮጵያ የካቶሊክ አቡን ተብሎ ተመርቆ በዚሁ ዓመት ከአንድ የኢጣሊያን ሚስዮናዊ ጋር ወደ ኢትዮጵያ ይህንኑ ሃይማኖት ለማስፋፋት ተላኩ ። ነገር ግን ፤ በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ በነበረው ታላቅ የካቶሊካውያን ጥላቻ ምክንያት ጦብያ እንኳን የካቶሊክን ሃይማኖት ለመስበክ ቀርቶ ፤ ካቶሊክ በመሆኑ በትውልድ ሀገሩ ለመኖር አደገኛ ስለሆነበት ወደ ካይሮ ተመልሶ በዚች በግብጽ ከተማ እስከ ዕድሜው መጨረሻ ተቀምጧል ።

በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ በኮሌጅዎ ኡርባኖ ትምህርት የሚከታተል ጊዮርጊስ ጋላባዳ የተባለ አንድ ኢትዮጵያዊ የሳንቶስ ስቲፋኖስ ገዳም ሃላፊ ሆኖ ፴፩ ዓመት ሠርቷል ። እዚያም በቆየበት ጊዜ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ለትምህርት ለማስመጣት በኢትዮጵያ የካቶሊክ ሃይማኖት መድከም ምክንያት ጥያቄው መልስ ሳያገኝ ቀርቷል ። ሆኖም ከ፲፰፻፴፰ ዓ.ም. በኋላ የካቶሊክ ሚሲዮን እንደገና በኢትዮጵያ ስለተቋቋመ በሚሲዮናውያን እየተላኩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደ ኢጣሊያ በተለይም ወደ ቫቲካን ለሃይማኖት ትምህርት መሄድ ቀጥለዋል ። በ፲፰፻፴፱ ዓ. ም. ደ. አባድየ የተባለው የፈረንሣይ ዐዋቂና ሀገር ተመልካች ከኢትዮጵያ ሲመለስ ወልደ ኪሮስ የተባለውን ወጣት ሮም ወስዶ ወደኮሌጅዎ ኡርባኖ አስገብቶታል ። ይህም ወጣት እስከ ፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ድረስ ሲማር ቆይቶ ተመልሶ ኢትዮጵያ ገብቷል ። በ፲፰፻፵ ዓ. ም. ወልደ ሥላሴ ፥ ኪዳነ ማርያምና ገብርኤል የተባሉ ኢትዮጵያውያን ሮም ሄደው እስከ ፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ድረስ በኮሌጅዎ ኡርባኖ ትምህርት ሲከታተሉ ቆይተው ፤ ተመልሰው ወደ ኢየሩሳሌም ሄደዋል ።

በ፲፰፻፵፩ ዓ. ም. ደ. ጃኮቢስ የተባለው በትግሬ የላዛሪስት ካቶሊክ ሚሲዮን መሪ የነበረው ወደ ሮም ሲመለስ

አራት ኢትዮጵያውያን ቀሳውስት ይዞ በኮሌጅዮ ኡርባኖ እንዲማሩ ተደርጓል ። እነዚህም የአክሱሙ ዘካርያስ (ዕድሜው ፲፰) ፣ የአራምባው ወልደ ገብርኤል (ዕድሜው ፴፫) ፣ የአድዋው ወልደ ሚካኤል (ዕድሜው ፲፭) ፣ የቦሬው ሚካኤል ዘውዴ ነበሩ ።

በ፲፰፻፴፩ ዓ. ም. ዴ. ጃኮቢስ በተጨማሪ አንድ ሃያ ዓመት የሚሆነውን ተስፋዬ የሚባል ኢትዮጵያዊ ኮሌጅዮ ኡርባኖ ትምህርት እንዲቀጥል ልኮት የተባለው ወጣት ሮም መድረስ አቅቶት ኔፕልስ ላይ ሦስት ወር ከአሳለፈ በኋላ ችግሩን የሚገልጽ የሚከተለውን ደብዳቤ ወደ ሮም ለጳጳሱ ልኮዋል ፤ ይህም ደብዳቤ ዛሬ በፕሮፓጋንዳ ፊዴ ኢትዮጵ ያን በሚመለከተው የታሪክ መዛግብት ክፍል ይገኛል ።

«ዛቲ መልክት ዘተስፋይ ኢትዮጵያዊ ፤ ዘስመ ሀገሩ ይሣ አቡነ አፍሴ ትብጻኅ ኀበ አቡነ ቅዱስ ፒዮ ኖኖ ጳጳ ሳት ዘኀሎ ፤ በመንበረ ጴጥሮስ ርእሰ ሐዋርያት ወሪ እሰ ቤተ ክርስቲያን ዘኀለወት በትምኅ(ር)ተ ወንጌል ቅዱስ ወአንተ ርእሳ ለዛቲ ቤተ ክርስቲያን ወሪእሶሙ ለኑዎላውያነ አባግዕ ከመ ኢይሶዶሙ አራዊት ።»

ጌታዬ ሆይ እነሆ የሃይማኖት ልጅ ነኝ ። አቡነ ያዕቆብ (ዴ. ጃኮቢስ) ሃይማኖት አስተምረውኝ ካቶሊክ ነኝ ። እነሆ ጌታ ሆይ አቡነ ያዕቆብ ወደ አውሮፓ ሂድ ተማር ብሎ ሰደውኝ ናጶሊ ተቀምጫለሁ ። ትምህርት አላገኘሁም ። አሁንም ጌታ ሆይ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር ብሎ ወደ ብሮባጋንዳ ከተማሪ ቤት እንዲያገቡኝ እለምኖአለሁ ። ጌታዬ ሆይ ይህን ነገር ይሁን ይሉኛል ብየ ተስፋ አለኝ ። እግዚአብሔር የመንግሥተ ሰማይ ዋና ያድርግሎ ። ዓሚን ፤ ናጶሊ ከገባሁ ስዎስ ወር አደ ረግሁ አሁም ጌታዬ ስምንት ወር ከአረማውያን ጋር በመከራ ነው የመጣሁ እና ይዘኑልኝ ጌታዬ ሆይ

ዘተስፋይ ኢትዮጵያ ዘስመ ሀገሩ»

ደብዳቤው ምን ዓይነት ምላሽ እንዳገኘ ለማወቅ ያደ ረግነው ሙከራ ውጤት ሳያገኝ ቀርቷል ።

ስለ ሳንቶ ስቴፋኖስ ገዳምና ስለ ኮሌጅዮ ኡርባኖ ያለ ንን ነገር ከመጨረሳችን በፊት ፤ አንድ ቃል ስለ ደብተራ ክፍለ ጊዮርጊስ ማስታወስ መልካም ይሆናል ። ደብተራ ክፍለ

ጊዮርጊስ ሮም የሄደው ወደ ፲፰፻፶፬ ዓ. ም. ግድም ሲሆን ወደ ፕሮፓጋንዳ ፊዴ ኮሌጅ ተልኮ ይማር አይማር ግልጽ አይደለም ። ሆኖም ይህንን ደብተራ በተለይ የምናስታውሰው ስለ ተከታተለው ትምህርት ሳይሆን ፤ በሳንቶ ስቴፋኖስ ገዳም ስለ አስተማራቸው ተማሪዎች ነው ። ከነዚህም አንዱ የታወቀው ኢግናዝዮ ጉዊድ ነበር ። ጉዊድ በዚያ ካፈራው ትምህርት በሁለት ቅጽ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸውን የ፲፯ኛውና የ፲፰ኛው ክፍለ ዘመን የአምስት የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ከግዕዝ ወደ ፈረንሣይ እንደተረጐመ ይታወሳል ።

እነዚህ በሮም የተማሩ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያ ተመልሰው ፤ ብዙዎቹ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው ፤ የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት እየዞሩ በመስበክ የአውሮጳን ሚስዮናውያን ይደግፉ ነበር ። ከነዚህም ውስጥ የታወቁት ወልደ ኪሮስ ፤ ወልደ ሥላሴ ፤ ኪዳነ ማርያም በተለይ ደግሞ አባ ዘካርያስ ናቸው ።

እንደሚታወቀው ሁሉ የሳንቶ ስቴፋኖስ ገዳም ከ፲፬፻፲፬ ዓ. ም. ጀምሮ ሮም የካቶሊክን ሃይማኖትና የፍልስፍናን ጥናት ለመከታተል ለሚሄዱ ወጣት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማረፊያ ሆኖ የቀድሞውን ታሪኩን እስከዛሬ ድረስ ለመቀጠል ችሏል ።

## በፈረንሳይ አገር የተማሩ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ፤

በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ አገር ለትምህርት የሚሄዱት ወደ ኢጣሊያ ብቻ ሳይሆን ወደ ሌሎችም የአውሮጳ አገሮች ነበር ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ ፈረንሣይ ነው ።

### ማኅደረ ቃል ፤

ወደ ፈረንሣይ አገር ለትምህርት ከሄዱት በቅድሚያ የታወቀውና ብዙም አውሮጳውያን በጽሑፋቸው የጠቀሱት ማኅደረ ቃል የተባለው የአድዋ ተወላጅ ነበር ። ለፌቭር የተባለው ፈረንሣዊ ኢትዮጵያን በጐበኘበት ጊዜ ማኅደረ ቃል አገር በማሳየትና በማናቸውም አገልግሎት ይረዳው ስለነበር በ፲፰፻፴፩ ዓ. ም. ለፌቭር ወደ አውሮጳ ሲመለስ ማኅደረ ቃልን ይዞት ሄደ ። በዚያን ጊዜም ማኅደረ ቃል የ፲፰ ዓመት ወጣት ነበር ተብሎ ይገመታል ። በፓሪስም እንደ

ደረስ የፈረንሣይ መንግሥት በዓመት ፪ሺ ፍራንክ ስኮላር ሸፕ (የትምህርት መተዳደሪያ) ፈቅዶለት ፤ ትምህርቱን ለመከታተል ችሏል ። የሆነ ሆኖ ይማርበት የነበረው ትምህርት ቤት የትኛው እንደነበር በግልጽ ሊታወቅ አልተቻለም ። በአንድ በኩል ያገኘናቸው ማስረጃዎች ወጣቱ የተማረው «አንሪ ካትር» በተባለው የመንግሥት ት/ቤት መሆኑን ሲገልጽ ፤ ሌሎች ደግሞ ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት አውሮጳውያን የላዛሪስት ካቶሊክ ሚሲዮናውያን በአሳሰቡት መሠረት ፤ በካቶሊክ ት/ቤት የሃይማኖት ጥናት ይከታተል ነበር የሚሉ ናቸው ። የሆና ሆኖ ማኅደረ ቃል በመጀመሪያ የመንግሥት ት/ቤት ገብቶ ፤ ሚሲዮናዊያን ከዚያ አስወጥተው ወስደው እነሱ ት/ቤት አስገብተውት ሊሆን ይችላል ። በመጨረሻም ከፈረንሣይ በ፲፰፻፵፰ ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ተነሥቶ ፤ እግረ መንገዱን ካይሮ ላይ የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን አጋጥመውት እንደገና ለትምህርት ወደ ማልታ የፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ ኮሌጅ ልከውት አራት ዓመት ቆይቷል ። ከዚያም ወደ እንግሊዝ አገር ሄዶ ሁለት ዓመት ካሳለፈ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል ።

ከላይ እንደጠቀስነው የካቶሊክ ሚሲዮኖች ከ፲፰፻፴ ዓ.ም. ወዲህ በፈረንሣይና በኢጣሊያ መንግሥት እርዳታ እንደገና በኢትጵያ ሲቋቋሙ ፤ እነሱን ለመቃወምና በኢትዮጵያ የፕሮቴስታንትን ሃይማኖት ለመትከል ሲሉ በእንግሊዝና በጀርመን የተደገፉ የፕሮቴስታንት ሚሲዮኖች በተከታታይ በኢትዮጵያ ተመሥርተው ነበር ። ይህም ስለሆነ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን በኢትዮጵያ የሃይማኖትና የፖለቲካ ትግል ሲያደርጉ ቆይተዋል ፤ ስለዚህ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ለወደፊት ቄሳውስት የሚሆናቸውን ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ አገር ለትምህርት ስለላኩ የፕሮቴስታንት ሚሲዮኖችም እንዲሁ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ወደ ውጭ እየላኩ አስተምረዋል ። አንዳንድ ጊዜም አንዱ ሚሲዮን ያስተማረውን ወጣት በትምህርት ቤት ሳለ ፤ ወይም እግረ መንገዱን ሲመለስ ወደ ኢትዮጵያ ሲያመራ ሌላው ሚሲዮን እየወሰደ ሃይማኖቱንና ትምህርቱን ወደ ሌላ ይለውጠዋል ። በማኅደረ ቃልም ደርሶበት ያየነው ይህንኑ ነው ።

ኢትዮጵያ ከተመለሰ በኋላ ማኅደረ ቃል የፕሮቴስታንት ሃይማኖት የሚሰጥበት ት/ቤት ከፍቶ ለጥቂት ጊዜ ሲሠራ

ቆይቷል ። ሆኖም ት/ቤቱ የሚያጠግብ ውጤት ባለመ ስጠቱ ትቶት ሳለ ፤ ዘመኑ ቴዎድሮስ የነገሡበት ጊዜ ነበ ርና ንጉሡ ማኅደረ ቃል ውጭ ሀገር ሄዶ መማሩን ባወቁ ጊዜ ጠርተውት ደብረ ታቦር ድረስ ሄዶአል ። ዐጼ ቴዎድ ሮስ ማኅደረ ቃልን ያስጠሩት በአውሮጳ የቴክኒክና የሜካ ኒክ ትምህርት ተምሮ መጥቷል ብለው በማሰብ ስለነበር ፤ የማኅደረ ቃል የሃይማኖትና የቋንቋ ዕውቀት እጅግም አላ ጠገባቸውም ተብሎ ቢጻፍም ፤ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዐጼ ቴዎ ድሮስን በአስተርጓሚነት ሲያገለግል ቆይቷል ። ማኅደረ ቃል ጥሩ አድርጎ የሚያውቃቸው ቋንቋዎች ፈረንሣይኛና እንግሊዝኛ ሲሆኑ ፤ በተጨማሪ መጠነኛ የኢጣልያንኛና የአረብኛ ቋንቋ ዕውቀት ነበረው ።

ዐጼ ቴዎድሮስም ከሞቱ በኋላ ማኅደረ ቃል የዐጼ ዮሐንስ አስተርጓሚ ሆኖ ሲሠራ ቆይቶ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ።

## በማርሴይ (ፈረንሳይ) አባ ማሳያ ያቋቋሙት የካፑቺን ኮሌጅ

በ፲፱ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ሁለት ዓይነት አቋም ያላቸው የካቶሊክ ሚሲዮኖች ተቋቁመው ነበር ። አንደኛው የትግሬው የላዛሪስት ካቶሊክ ሚሲዮን ሲሆን ፤ ሁለተኛው ደግሞ የጋላ ሚሲዮን ተብሎ ይጠራ የነበረውና በአባ ማሳያ ይመራ የነበረው የካፑቺን ካቶሊክ ሚሲዮን ነበር ። ይህም ሚሲዮን የተቋቋመው በሸዋ አካባቢ በሚገ ኙት ክፍለ ሀገሮች ነበር ።

ከዚህ በላይ እንዳየነውም ሁሉ ወደ ጣሊያን ሀገር ኢትዮጵያውያንን እየላኩ ያስተምሩ የነበሩት የትግሬው የላ ዛሪስት ካቶሊክ ሚሲዮናውያን ነበሩ ። ይህም ስለሆነ የካፑ ቺኑ ሚሲዮን አለቃ አባ ማሳያ በ፲፰፻፷፮ ዓ.ም. በማርሰይ ከተማ አንዲት ትንሽ ኮሌጅ አቋቁመው ፤ ኢትዮጵያውያን ፤ በተለይም ጋሎች ወጣቶችን ፤ ለትምህርት ለመላክ ወሰኑ ። ለዚህም ትምህርት ቤት የሚሆኑትን ወጣቶች ማሳያ በ፲፰፻፷፮ ዓ. ም. መጨረሻ ላይ ምፅዋ ሄደው ከባሪያ ነጋዴዎች በገንዘብ የገዟቸው ሕፃናት ነበሩ ። አባ ማሳያ ይህን ያደረ ጉበት ምክንያት ኢትዮጵያውያን ቤተ ሰቦች ልጆቻቸውን አልሰጥም ስላሉ ይሁን ወይም በባርነት የተሸጡትን ነፃ ለማውጣት ይሁን አይታወቅም ። የሆነው ሆኖ አባ ማሳያ ዐሥር የሚሆኑ ሕፃናት ለእያንዳንዳቸው ከአርባ እስከ አርባ

አምስት ብር ከፍለው ፤ አጥምቀው አዳዲስ ስም ሰጥተው ወደ ማርሰይ ሰደዋቸዋል ። ከነዚህም ሕፃናት ውስጥ ስድ ስቱ ጉራጌ ሲሆኑ ሁለቱ የሊሙና የኖኖ ጋሎች ፤ አንድ ከኩሎ ፤ አንድ ከጂንጀሮ ነበሩ ። ስማቸውም ሉዊስ ፤ ማር ቆስ ፤ አልበርት ፤ ያዕቆብ ፤ ዮሐንስ ፤ አንቷን ፤ ፍራንሷ ፤ ጴጥሮ ስና ዮሴፍ ተብሏል ። እነዚህም ዐሥር ተማሪዎች ማርሴይ በጥር ፲፰፻፰፯ ዓ.ም. ደርሰው ፤ በቅድሚያ እዚያ ከሚጠብ ቋቸው ሁለት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ከሚካኤልና ከእስ ጢፋኖስ ጋር በጠቅላላው ፲፪ ሆነው ትምህርት ጀምረዋል። ትምህርቱም በሞላ ጎደል የሃይማኖትና የፈረንሣይ ቋንቋ ልምምድ ነበር ። –

ሆኖም ወደ ፲፰፻፰፯ ዓ. ም. መጨረሻ የኮሌጁ አስተ ዳዳሪዎች የተማሪዎቹ ቁጥር አነሰብን በማለት በማርሰይ ከሚገኙት ሚሲዮናውያን አንዱ ፤ ተጨማሪ ተማሪዎችን ለማግኘት ወደ ምፅዋ ለመሄድ ተነሥተው ፤ እዚያ ሳይደርሱ እግረ መንገዳቸውን ካይሮ ላይ ከኢትዮጵያ በባርነት ተሸ ጠው የመጡ ዘጠኝ ልጆች አግኝተው ገዝተው ወደ ማር ሴይ ተመልሰዋል ። ከነዚህም አንዱ ብቻ አማራ ሲሆን ከቀ ሩት የታወቁት ፤ አንድ ከሊባን ፤ አንድ ከጅማ ፤ አንድ ከጉ ድሩ ፤ አንድ ከጉራጌ ነበሩ ። እነዚህም እንደ ቀድሞዎቹ ተጠ ምቀው አዳዲስ ስም ተሰጥቶዋቸዋል ። እነርሱም አልፎንስ ፤ አውግስቶስ ፤ ሻርልስ ፤ ገብርኤል ፤ ጊዮርጊስ ፤ ሄንሪ ፤ ማርዮስ፤ ጳውሎስ ፤ ፌሊጶስ ፤ የተባሉ ነበሩ ።

የማርሴይ ኮሌጅ ዕድሜው በጣም እረዥም አልነበረም። ስለዚህም በተጀመረ በሦስተኛው ዓመት በገንዘብ ማጣር የተ ነሣና ኮሌጁ ተዘግቶ በውስጡ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የካፑቺንን ሚስዮን ለመርዳት ወደ ሸዋ ተመልሰዋል።

ተመለሱም ብንል በሙሉ አልተመለሱም ፤ ከነሱ መሃል አንቷን የሚባለው የኖኖ ጋላ ተወላጅ በሕመም ምክንያት በማርሴይ ሕይወቱን አጥቷል ። አንቷን ከላይ እንዳየነው በ፲፰፻፰፯ ዓ. ም. አባ ማሳያ ምፅዋ ከገዟቸው ልጆች አንዱ ነበር ። በዚያም ጊዜ ፲፰ ዓመት ይሆነው ነበር ተብሎ ይገ መታል ። በዕውቀቱም ከሁሉ የላቀ ነበር እየተባለ በአስተ ማሪዎቹ ተጽፎለታል ። ይህም ስለሆነ አባ ማሳያ የካቶሊ ክን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ለማቋቋምና ለማስፋፋት እንዲ ሁም የማርሴይ ኮሌጅ ለማቋቋም ለረዳው ለአንቷን ደአባ ድየ ባለውለተኛነታቸውን ለመግለጽ ሲሉ ፤ የዚህን ልጅ ስም አንቷን ብለው ለደአባድየ የክርስትና ልጅ እንዲሆነው ሰጥ

ተውታል ። በዚህም ምክንያት ደአባድየ የክርስትና ልጁን በየጊዜው ማርሰይ እየመጣ ከመጠየቁም በላይ በሁለቱ መሀከል የደብዳቤ መጻጻፍ አላቋረጠም ነበር ። ደአባድየም ልዩ ልዩ የኢትዮጵያውያን ቋንቋዎች (ግዕዝ ፤ አማርኛ ፤ ትግሬኛና ጋልኛ) ከማወቁ የተነሣ ከአንቷን ጋር በጋልኛ ደብዳቤ ይጻጻፍ ነበር ። እነዚህም ደብዳቤዎች ዛሬ በፓሪስ ብሔራዊ መጻሕፍት ቤት በኢትዮጵያ ታሪክ ክፍል ይገኛሉ ። ከእነዚህም አንዱን ለአንባቢው ማቅረብ ምናልባት ጠቃሚ ሳይሆን አይቀርም ።

አንቷን ለደአባድየ ፤

> አታም ጅርቱ እኔ ኢሲኒ እንራፉኔ እኮ ኢሲኒ ካን ናፍጄታኔ ቢያኮድፍታኒ ሃዳኮ አፋን ጋላ እንቤክቱ ማሌ፤ ሴላካን እሺን ጋማዱቲ ጋሪ ቲታቤ እርጋ ቱሬ ። ዮ እኔ አፋን ፍራንሴ ሳናን ቤካ ፤ ጋኔ ኪታቤ እርጋ ቱሬ ። ሀማ እንቤኩ ቲኖ ማሌ ቤካ ። ቤኩፍ ጂራ ። ዮ ዋቃዮ ና ቤሊስ ። ባቀዮው ቢያ ጋላቲ ባኤ ቱኔ ኢሲኒ እንቤኩ ቱሬ ዋቀ ዮ ኢሲኒ ና ቤኪሲስ ጋላቲ ዋቃዮ አጋኝ አጋኝ አካ እባኮ ኤማኑኤል[2] ቤራቱ አቶ ጋሪ ጊርኒ አማና ጌኛ ፤ ኢሲኒ ኮታ አባ ላ ቂኬኛ ኢላላ ።

አንቷን ይህንን ደብዳቤ የጻፈው በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ሲሆን በዚሁ ዓመት ባደረበት የሕመም ምክንያት ማርሴይ ከተማ መሞቱ ታውቆዋል ።

ከማርሴይ ሸዋ ከተመለሱት ወጣቶች መሃል አብዛኛዎቹ የካቶሊክ ቀሳውስት ሆነው አውሮጳውያንን ሚሲዮናውያን ሲረዱ ፤ ሌሎች ደግሞ ለአጼ ምኒልክና ለመኳንንቶቻቸው እንዲሁም ለአውሮጳውያን ጐብኚዎች በአስተርጓሚነት እየተቀጠሩ ሠርተዋል ። ከነዚህም መሃል በጣም የታወቀው ዮሴፍ (የገላኑ) ወይም ዮሴፍ[3] ጭንቅሎ ነው ። አቶ ዮሴፍ ለብዙ ጊዜ የአጼ ምኒልክ አስተርጓሚ ሆነው ሲሠሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻም በጅቡቲ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ቆንስል ሆነው ተሹመው ለብዙ ዘመን አገልግለዋል ። የአቶ ዮሴፍም የልጅ ልጆች ዛሬ በአዲስ አበባ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይገኛሉ ።

---

2. የትምህርት ቤቱ ዲሬክተርና ዋናው አስተዳዳሪ አባ አማኑኤል ነበሩ ።
3. ግራዝማች ዮሴፍና አቶ ዮሴፍ የተለያዩ ናቸው ።

# የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን በውጭ አገር ያስተማሩዋቸው ኢትዮጵያውኖች

ከላይ እንደጠቀስነው ከ፲፰፻፴ ዓ. ም. በኋላ የካቶሊክ ሚሲዮኖች እንደገና በኢትዮጵያ በተቋቋሙ ጊዜ ፤ በተከታታይ የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሃይማኖታቸውን ማስፋፋት ጀምረው ነበር ።

ከነዚህም አውሮጳውያን የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ጥቂቶቹ ከኢትዮጵያ ለቀው በሚሄዱበት ጊዜ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች እየያዙ ሄደው ወደ ልዩ ልዩ ሥፍራ ለትምህርት ሰደዋቸዋል ። ሆኖም ብዙውን ጊዜ የሚሄዱት ወደ እንግሊዝ ቅኝ አገሮች ነበር ። ከነዚህም ፕሮቴስታንት ትምህርት ቤቶች ከተላኩት ኢትዮጵያኖች በቅድሚያና በይበልጥ የምናውቃቸው የአቶ ወርቄን ልጆች ነው ።

## የአቶ ወርቄ ልጆች ፤

አቶ ወርቄ ትውልዳቸው አርመን ፤ የቀድሞ ስማቸው ጋራቤት ነበር ። ተግባራቸውም የወርቅ ሥራ ሲሆን ፤ ወርቄ የሚባለውን ስም የወሰዱት ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ነው ። አቶ ወርቄ ወደ ኢትዮጵያ መቼ እንደመጡ ባይታወቅም ፤ ወደ ፲፰፻፺ ዓ. ም. አቅራቢያ መሆኑ ይገመታል ። የሆነው ሆኖ አንዲት ኢትዮጵያዊት አግብተው ምርጫ እና ገብሩ የተባሉትን ልጆች ወልደዋል ።

አቶ ወርቄ ሁለት ልጆቻቸውን ገብሩና ምርጫ ቦምቤ በሚገኘው የስኮትላንድ ፕሮቴስታንት ሚስዮን ተብሎ ወደ ሚጠራው የዶክተር ዊልሰን ት/ቤት ልከው ማስተማራቸው ሲታወቅ ፤ መቼ እንደላኳቸው ግልጽ አይደለም ። ነገር ግን ገብሩና ምርጫ ከ፲፰፻፺፮ ዓ. ም. በፊት ፤ ማለት ቴዎድሮስ ከመንገሣቸው በፊት ፤ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ነበር ።

ሁለቱም ልጆች ኢትዮጵያ እንደደረሱ የፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን እንደመከሩዋቸው ፤ በትግሬ የዚሁ ሃይማኖት ማስፋፊያ የሚሆን ት/ቤት ከፍተው ሕፃናትን ለማስተማር ሲዘጋጁ ፤ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስትና አለቆች ስለተቃወሙአቸው ት/ቤቱ ተዘጋ ።

ከዚያም ቴዎድሮስ በ፲፰፻፺፮ ዓ. ም. እንደነገሡ ምርጫ ወርቄ ንጉሡን በአስተርጓሚነት ሲያገለግል ቆይቷል።

እንደሌሎቹ የፕሮቴስታንት ሚሲዮኖች እንዳስተማሯቸው ልጆች ሁሉ የአቶ ወርቄ ልጆች ምርጫና ገብሩ ፈረንሣይና እንግሊዝ በኢትዮጵያ በሚያደርጉት የፖለቲካ ትግል ፤ እስከ መጨረሻው የእንግሊዝ ፖሊቲካ ደጋፊዎች ነበሩ ። የእንግሊዝ ጦር አጼ ቴዎድሮስን ለመውጋት በመጣ ጊዜ ለእንግሊዞች በአስተርጓሚነትና በመንገድ አሳይነት አገልግለዋል ።

አጼ ቴዎድሮስም ከሞቱ በኋላ በዚሁ በአስተርጓሚነት ለአጼ ዮሐንስ ከማገልገላቸውም በላይ በኢትዮጵያ የእንግሊዝን ፖሊቲካ በመደገፍ ፈረንሣይን መቃወም ቀጥለው ነበር ።

የገብሩ ወርቄም ልጆች መሸሻ ወርቄ ፤ ብሩ ወርቄና ዮሐንስ ወርቄ[4] ወደ ዶክተር ዊልሰን ፕሮቴስታንት ት/ቤት ቦምቤ ተልከው ፤ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆይተው ከ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. በፊት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በአስተርጓሚነት ማገልገል ቀጥለዋል ። በ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. አጼ ዮሐንስ ከእንግሊዝ ጋር ውል ሲዋዋሉ ፤ የእንግሊዝን ፖሊቲካ በጣም ደግፈው ለንጉሡ አቅርበው ውሉም ከተፈረመ በኋላ ምርጫ ወርቄ ፤ መሸሻ ወርቄና ልጅ ብሩ ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው ሄደው ነበር ። ሁለቱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሲመለሱ ትንሹ ብሩ ወርቄ ትምህርት ለመቀጠል እዚያው ቀርቷል ። እርሱም በእንግሊዝ አገር ሦስት ዓመት ያህል ከቆየ በኋላ በ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. ወደ አገሩ ተመልሷል ።

<u>ወልቃይት ብሩ ፤</u>

ብሩ ጴጥሮስ የተወለደው በወልቃይት (ትግሬ) ውስጥ ስለሆነ ፤ ብዙውን ጊዜ የሚታወቀው ወልቃይት ብሩ በሚለው ስም ነበር ። ብሩ የአማርኛና የግዕዝ ቋንቋ ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ገና ልጅ ሳለ ፤ የፈረንሣይ ተወላጅ አንቷን ደ አባድየ ኢትዮጵያን ጐብኝቶ ወደ አገሩ በ፲፰፻፺፰—፺፱ ዓ. ም. ሲመለስ ብሩንና የብሩን አጐት አለቃ ተወልደ መድኅንን አስከትሎ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ነበረ ። ደ. አባድየም ብሩንና አለቃ ተወልደ መድሕንን ኢየሩሳሌም በሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ኤል ሱልጣን ትቶ ወደ ፈረንሳይ ተመልሶአል ። ከዚህም በኋላ አለቃ ተወልደ መድኅንና

4. ወርቄ የቤተሰብ ስማቸው ሆኖ የተወሰደ ይመስላል ።

ሌሎችም የኢትዮጵያ መነኮሳት እንደቀድሞው በርስቱ ጉዳይ ከሚከራከርዋቸው ኢየሩሳሌም ከሚገኙት ከአርመንና ከግ ብፅ መነኮሳት ጋር ተጣልተው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ አለቃ ተወልደ መድኅን ብሩን አርመን ት/ቤት አስገብ ተው በነሐሴ ፳ ቀን ፲፰፻፵፱ ዓ. ም. ከኢየሩሳሌም ተነሥ ተው ግብፅ ደብረ መሐረክ ወይም ደብረ ቁስቋም የሚባል ገዳም ገብተዋል ። ከዚያ በኋላ ብሩ በኢየሩሳሌም ከሚገ ኘው የአርመን ትምህርት ቤት ገብቶ አንድ ዓመት የአር መን ቋንቋ ሲማር ከቆየ በኋላ ፤ ያስተምረው የነበረው የአር መን ጳጳስ ስለሞተ ፤ አመት ያህል ያላንዳች ትምህርት ተቀመጠ ። ከዚህ በኋላ በኢየሩሳሌም የፕሮቴስታንት ሚሲ ዮን ጳጳስ፡ ሆነው የተሾሙት ቀደም ብለው ኢትዮጵያን ለብዙ ዓመታት ጐብኝተዋት የነበሩት ሳሙኤል ጐባት ፤ ብሩን የርሳቸው ሚሲዮን በሚያካሂደው ትምህርት ቤት አስገቡት ። በዚህም ት/ቤት ብሩ ጥቂት የአረብኛ ቋንቋ ለመማር ችሏል ። የሆነ ሆኖ ወልቃይት ብሩ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በሳሙኤል ጐባት አማካይነት ኢየሩሳሌምን ለቆ ወደ ማልታ የፕሮ ቴስታንት ኮሌጅ ለትምህርት ሄዶአል ። እዚያም የደረሰው በ፲፰፻፶፩ አጋማሽ ነው ። ወልቃይት ብሩ በማልታ ሆኖ ለአንቷን ደ አባድየ የጻፋቸውን ከአሥራ አምስት በላይ የሆኑ ደብዳቤዎች ፓሪስ ብሔራዊ መጽሐፍት ቤት ከሚገ ኘው የደ አባድየ የታሪክ መዛግብት ለማግኘት ችለናል ።

በማልታ ኮሌጅ ወልቃይት ብሩ የሚያደርገው ጥናት በተለይ ስለ ቋንቋዎች ነበር ። እነዚህም ቋንቋዎች እንግሊ ዝኛ ላቲን አረብኛና ፈረንሣይኛ ነበሩ ። ከቋንቋም ሌላ የዓ ለም ታሪክ ቁጥር (ከቆየም በኋላ ጂኦሜትሪና አልጀብራ) ጂኦግራፊና የሃይማኖት ትምህርት ይወስድ ነበር ። በአንድ ደብዳቤም እንደገለጸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከሁሉ አጥብቆ የሚወደው ነበር ። ከ፲፰፻፶፩ ዓ. ም. በኋላ የአረብኛ እንዲሁም የአልጀብራና የጂኦሜትሪ አስተማሪዎች በመሄዳ ቸው እነዚህን ትምህርት ሲያቋርጥ እንዲሁም የፈረንሣይኛ ቋንቋ ስለከበደው ትቶታል ። በጠቅላላውም ሲነገር ከ፲፰፻፶፬ ዓ. ም. ጀምሮ የአስተማሪዎችና የተማሪዎች ቁጥር እየተቀነሰ የትምህርቱ አሰጣጥ እየተዳከመ በመሄዱ ብሩ በደብዳቤዎቹ ደጋግሞ ያማርር ነበር ። ትምህርቱንም በ፲፰፻፶፰ ዓ. ም. ለማቋረጥ ዋና ምክንያት የሆነው ይህ ነው ።

በማልታ የወልቃይት ብሩ የተማሪነት ኑሮ የችግር የነ በረ ይመስላል ። በአንድ ደብዳቤ ላይ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል።

«ከደሴቱም ከዓመት ይበልጣል ዙሬ አላውቅም ። ከባርም በሁለት ሰንበት በሶስት ሰንበት አንድ ጊዜ እሄዳለሁ ። ገንዘብም በወር ሁለት ሺሊንግ ይሰጡኛል ። መልካም መጽሐፍ መግዛት እፈልጋለሁ ድህነቴ ብቻ አሸግሮኝ እንጅ» ። ሆኖም ምግብና ልብሱ በነፃ ይሰጠው ነበር ።

ከዚህ ሌላ ወልቃይት ብሩ በማልታ አንዳንድ ጊዜ ብቸኛነት ይሰማው ነበር ። ገና ማልታ እንደደረሰም «እኔ ግን እጅግ አዝኛለሁ ። ካገር ከወዳጅ ካጎት ተለይቼ በመኖሬ በዚች ደሴት ዳሩ ግን ምን ይሆን ትምህርት በመውደዴ ከዚህ አደረሰኝ» በማለት ጽፏል ። በሌላ ደብዳቤ ደግሞ ያጋጠሙትን የኑሮ ችግሮች ሲገልጽ ፤ ስለ እንግሊዞች አስተማሪዎች እንዲህ ብሎ ጽፏል ። «መጀመሪያ ያጎቴ ናፍቆት የዘመዶቼ ወሬ ሁለተኛ የእንግሊዞች ጠባይ አልወደድሁትም ምነው ቢሉ የንግዳ ፍቅር የሌላቸው ኩሮች አዳሎች» ናቸው ። የወልቃይት ብሩ ሀዘን እመጨረሻው ወሰን የደረሰው ግን በ፲፰፻፶፬ ዓ. ም. መጨረሻ የአጎቱን የአለቃ ተወልደ መድኅን በደብረ መድረክ መሞት ከሰማ በኋላ ነው ። በዚህም ጊዜ እንዲህ ሲል ጽፏል።

«ስለ ደብተራ ተወልደ መድኅን ልቤ እንደ ሰም ቀለጠብኝ አይኔም ፈዘዘብኝ ታላቁ ዓለምም እንደ ትንሽ ጉድጓድ (ሆነብኝ) ። ... ወዳጅዎ ተወልደ መድኅን ሞቱ ። ወዴት ልሂድ ምን ላድርግ...»

በሃይማኖት ጉዳይ ፤ ወልቃይት ብሩ የሃይማኖት አስተማሪዎቹን ዕምነት ማለት የፕሮቴስታንት እምነት የተቀበለ ይመስላል ። ሆኖም ታላቁ ወዳጁና ደጋፊው የፈረንሣይ ተወላጅ አንቷን ደ አባድየ ጠንካራ ካቶሊክና በአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የካቶሊክን ሚሲዮን በኢትዮጵያ ለማስገባት መሣሪያ የሆነ እርሱ ስለነበር ብሩን ደጋግሞ የሚጠይቀው በማልታ ያሉት ፕሮቴስታንት ሚሲዮናውያን ሃይማኖታቸውን እንዲቀበል አድርገውት እንደሆን ነበር ። ብሩም ለደ አባድየ የሚሰጣቸው መልሶች «አዎን» ወይም «የለም» ብሎ ከመመለስ ለማምለጥ የተዘጋጁ ይመስላሉ ። የሚሰጣቸውም መልሶች ይህን የመሳሰሉ ነበሩ ።

—«የሃይማኖት ነገር ያሉኝ እንደሆነ ከዚኽ ስፍራ ኩሉ እንደ ፈቃዱ ነው ። እጅግም ሰዎች የልዩ ልዩ ሃይማኖት አሉ ። ከስላሞች ሳይቀር ። ያንተ ሃይማኖት ያሉኝ እንደሆነ ።

እኔ አምናለሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል የተወለደውን ። በሐዋርያትም ጉባኤ ። በመጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔር ቃል ።» …

—«በሃይማኖት እንዴት ነህ ብሎ ጠየቁኝ ። በእንግሊዝ ሃይማኖት ገብቸአለሁ ብል እንሆ በእግዚአብሔር ፊት ነው ውሸት እናገራለሁ ። አልገባሁም ብየ ብልም ደግሞ ውሸት ነው ። ይህንንም ማለቴ ስለዚህ ነው ። እጅግ ነገር ነገር አለ እነዚያም የሚሉት ለኔ የማይስማማ ። እጅግም አለ እኔ የምወደው ። ስለዚህ ጌታው ለነዚህ ሰዎች እኔ በላንት ሃይማኖት ገብቻለሁ ብል ወይም ለርስዎ መጥቼ በካቶሊክ ሃይማኖት አምናለሁ ብየ ብል በፍጹም ልቤ ካልሆነ ሰው ሊያምነኝ አይገባም ።»

በመጨረሻ በ፲፰፻፶፰ ዓ. ም. ብሩ ወደ ሀገሩ ለመመለስ ፈልጐ የመሄጃ ገንዘብ አስተማሪዎቹን ቢጠይቃቸው ወዳጅህ ደ አባድየ ይስጥህ ስላሉት ከዚህ የሚከተሉትን ደብዳቤዎች ለደ አባድየ ከጻፈ በኋላ ደ አባድየ ፪፻ ፍራንክ ልኮለት ከማልታ ወደ ግብፅ ሄድዋል ።

<u>፩ኛ ደብዳቤ ፤</u>

«ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ ብሩ ትብጻሕ ኀበ ክቡር አንጦንዮስ ዘአባድየ ። እንዴት ሰነበቱ የኔታ አንጀቴ ። የርስዎ ወረቀት ባነበብሁ ጊዜ እኔ በሳዘንሕዎ እጅግ አጥብቆ ከፋኝ። በፊተኛ ደብዳቤዎ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ *ሥጋና* ደሙ ተናገሩ ካቶሊኮች ይላሉ ቁርባኑን በቄስ ሲቀደስ የክርስቶስ *ሥጋና* ደም ፍጹም ሁኖ ይለወጣል ። ፕሮተስታኖች ግን በዚህ አያምኑም አሉኝ ። ይህ ክርክር በካቶሊኮችና በፕሮተስታኖች ብቻ አይደለም በሀበሻ ሳለሁኝ እጅግ ደብተሮች ሲከራከሩ ስሰማ ነበርሁና እንዲህ ያለ ክርክር መፍረድ ለኔ ለደንቆሮው አይገባኝም የሊቃውንት *ሥራ* ነው ብየ ለዚህ ምላሽ አልጻፍሁልዎ ። አሁንም ለኔ ይህ ነው የሚገባኝ ለማመን እርሱ በራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ *ሥጋው*ና ደሙ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ብሎ ሰጣቸው ። ወንጌለ ሉቃስ ምዕራፍ ፳፪ ወነሥአ ኅብስት ወአኰቶ ፈተተ ወወሀቦሙ ወይቤሎሙ ዝንቱ ውእቱ *ሥጋየ* ዘይትወሀብ በእንቲአክሙ ቤዛ ብዙኃን ወከመዝ ግበሩ ተዝካርየ በእንቲአየ ። ወከማሁ ጽዋዐኒ እምድኅረ ተደሩ ወይቤሎ ዝንቱ ጽዋዕ ዘሐዲስ *ሥርዐት* ውእቱ ዘበደምየ ዘይትከዐው በእንቲአክሙ

ወበአንተ ብዙኅን ። በሃይማኖትህ እንዴት ነህ ብሎ ጠየ ቀኝ በእንግሊዝ ሃይማኖት ገብቼ አለሁ ብል እንሆ በእግዚ አብሔር ፊት ነው ውሸት እናገራለሁ አልገባሁም ብዬ ብልም ደግሞ ውሸት ነው ። ይህንን ማለቴ ስለዚህ ነው እጅግ ነገር አለ እነዚያ የሚሉት፥ ለኔ የማይስማማ እጅግም አለ እኔ የምወደው ስለዚህ ጌታው ለነዚህ ሰዎች እኔ በላ ንት ሃይማኖት ገብቻለሁ ብል ወይም ለርስዎ መጥቼ በካቶ ሊክ ሃይማኖት አምናለሁ ብየ ብል በፍጹም ልቤ ካልሆነ ሰው ሊያምነኝ አይገባም ። እኔ አውቃለሁ እርስዎ ሊቅ ፊሎስፋ ነዎ ይህ ማለቴ አይሸ (ሽ)ግም የሰው ልብ እንዴት ስውር መሆኑ ። ዳሩግን ጌታው ለኔ እንዲሁም ለሁሉ ክር ስቲያኖች እንድንፋቀር ይገባናል ምነው ክርስቶስ ያንድ ልጆች አድርጎናልና እኛም እርሱ ለአባታችን እንዲህ ብለን እንጸልያለን አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ።

«እርስዎ እውነትዎ ነው መልካም መምህር ወደ ማልጣ እንዳይመጣ ። እንሆ ሁለት ዓመት ሶስት ዓመት እንግሊዝ አስተማሮች ከሄዱ ከስፍራቸው ሌሎች አላመጡም ብቻስ ከ pupil teacher በቀር እድሜቸው ፲፯ ፲፰ የሚያህል እንዲያውም ማስተማር የማያውቁ ። እኔም አልጀብራ ላቲን ታሪክም ሌላ ትምህርት ካመት ይበልጣል አስተማሪ ስለመ ታጣቱ አልማርም ። አሁን ተማሮቹ ፵፯ የሚበዙት ጽርያት ናቸው ። አስተማሮች እኒህ ናቸው ። ፈረጅ ናምሳዊ ኢጣልን ጽርእ ቱርክም ፫ እንግሊዝ pupil teacher ፪ አይነተኞች ማስተማር የማይወዱ በነዚህ ኮሌጅ ተበላሽቶ ያለ ። ከነ ዚህ ሁሉ ሰዎች እኒህ ዘንድሮ የሚሄዱ ናቸው ። ፫ አስተማ ሮች ሁሉ pupil teacher ፳፯ ተማሮች ። እኔም መሄድ እፈልጋለሁ ወዴት እምሄድበት አገር ግን ጨንቆኛል ወዳ ገሬ እንዳልሄድ ገንዘብ የለኝም ።

ለወንድሞችዎ እጅ እነሳለሁ ።

እግዚእር ለርስዎ ጤና እድሜ ይስጥ ። አሜን ።

ተጽሕፈት በዕለተ ሐሙስ አፕሪል ፱ ፲፰፻፶፯ እም ዓመተ ምሕረት ።

ተጽሕፈት በማልጣ ።

<u>፪ኛ ደብዳቤ ፤</u>

«ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ ብሩ ትብጻሕ ኀበ ክቡር እንጦንዮስ ዘአባድየ እጅጉን እንዴት ሰነበቱ፥ የኔታ እንጀቴ ባርያ እጅግ አጥብቄ ተጨንቄ አለሁ ። ተማሪ

ቤቱም አያሌ ጊዜ እንደነገርሀዎ ከሶስት ዓመት ጀምሮ ዝቅ እያለ ሄደ ። ዘንድሮ ግን እንዲው ከፋኛ ሁኖ ነበረ ስለ ዚህም እጅግ ጳላቶች ተነሥተው በጽፈታቸው ተማሪ ቤቱን እጅግ አጥብቆ ገሠጹ እንዲውም በልባቸው አሰቡ ተማሪ ቤቱ እንዲነቀል ፈቀዱ ። ዳሩ ግን ማኅበሩ ከእንግጣር የሚ ኖሩ ይህን ሰምተው ሁለት አስተማሮች ሌሎችም ሁሉ አሰ ናበቱ ሌላ አይነተኛ ገና አልሰደዱም ። እኔ ግን የርስዎ ወረ ቀት ከተቀበልሁኝ በኋላ ሊያሰናብቱኝ ብዬ ሁለት ወረቀት ወደ እንግሊዝ አገር ጻፍሁኝ ዳሩ ምላሹ ግን አልመጣ ልኝም ። ስለዚህ ነው ለኔ መሰደድ የማይወዱ ። አንድ የሀ በሻ አሽከር ከኛ ተማሪ ቤት ይማራል ብሎ ከሕዝቡ ዘንድ ገንዘብ ማጠራቀም እንዲቀናቸው ተሎ ብሎ የሚያሰናብ ቱኝ አይመስለኝም ። እርስዎም ለመንገድህ ገንዘብ እሰድልህ አለሁ ብሎ ተስፋ ባስደረጉኝ ጊዜ ተነሥቼ እሔድ ብዬ ነበርሁ ዳሩ ግን በሁለት ነገር እንዳልሄድ ዘንድ ተከለከል ሁኝ ። መጀመሪያም የኔ pass port በጄ አለመሆኑ ። ሁለተኛ ውም እሄን ያህል ዘመን ከነዚህ ጋራ ተቀምጬ እንበለ certificate እንደ ሌባ ተሰርቄ እሔድ ዘንድ አይገባም ብየ ለነዚያ መጻፍ ጀመርሁኝ ።

እኔ ጌታዬ አሁን የማደርገው ነገር ጨንቆኛል በዚህ ስፍራ በግዞት የተጠበቅሁኝ ይመስለኛል ። በዚህ ስፍራ ትምህርት የሚጠቅሙኝ ወይ ጥበብ የሚያስተምሩኝ ቢሆኑ እንዲሁ አላዝንም ነበር ። ዳሩ ግን ጊዜያቴ በከንቱ ስለ አለፈ ልቤ ይነደኛል ።

ጌታዬ ተስፋ ስለ ሰጡኝ እግዜር ደጉ አምላክ ከዓለም እድሜና ጤና ከሚመጣው ዓለምም ገነት ተድላ ይስጥዎ አሜን ። ለወንድሞችዎ እጅ እነሳለሁ ።

ተጽሕፈት በማልጣ ስፕቴምበር

የመንገዱ ዋጋ ከማልጣ ወደ እስክንድርያ ይህ ነው ።

| | |
|---|---|
| First class | £ 9 |
| Second class | £ 6 |
| Third class | £ 4 |

<u>፫ኛ ደብዳቤ ፤</u>

ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምኀበ ብሩ ዘኢትዮጵያ ትብ ጻሕ ኀበ ክቡር እንጦንዮስ ዘአባዲየ ። የርስዎ የተወደደ ወረ

ቀት በጌታ ሮጀር እጅ የሰደዱልኝ በደረሰኝ ጊዜ እጅግ አጥ ብቆ ደስ አለኝ ። የጢስ መርከቡ በሁለት ሰዓት በኋላ ሊለቅ ስለሆነ እኔም ያልተሰናዳሁኝ ስለሆንሁኝ ከመስየ ሮጀር ጋራ መሔድ ዘንድ አልተቻለኝም ።

እነዚህ ሰዎች ይሰዱኝ አይወዱም ያልዎ በፍቅር ማለቴ ነው ። በጸቡ ግን አንድ ሰው አትሂድ ብሎ የሚከ ለክ(ለ)ኝ የለም ። ዳሩ ግን እኔ እሒነን ያል ዓመት ከነዚህ ጋራ ተቀምጬ በበጉ እንድላቀቅ እወዳለሁ ።

አንድ ነገር ብቻ አስጨንቆኛል እንጅ ያነንም ያገሩ ሰዎች ባዩኝ ጊዜ በተረት እንዲህ እንዳይሉኝ ። ጎንደር ወጣህ ምን አመጣህ ።[5] ስለዚህም ጌታው እለምነዎ አለሁ ፈቃደዎ እንደ ሆነ ይዘዙኝ ወደ ፍራንስ እኔ ዘንድ ከዚያም ጥበብ ተምሬ ወይ ትምርት ገፍቼ ወደ አገሬ እመለስ ዘንድ ፈቃደዎ ያልሆነ እንደሆነ ግን እግዜር ያመስግንዎ በሰደዱ ልኝ ገንዘብ ቶሎ ብየ አገሬ እገባለሁ ። ላምላክም ሁልጊዜ እለምነውአለሁ በኔ መልካም ስለ አደረጉ ውለታዎም በዚህ አለም ክብርና ጤና ። በሚመጣውም መንግሥተ ሰማያት አሜን ። ለወንድሞችው እጅ እነሳለሁ ።

ተጽሕፈ ት በማልጣ ። Nov. 25th. 1857.

ከዚህ በኋላ ወልቃይት ብሩ ደ አባድየ በላከለት ገን ዘብ ከማልታ ተነስቶ ወደ ግብፅ ሄድዋል ። ግብፅም እን ደደረሰ የሚከተለውን ደብዳቤ ጽፈዋል ።

«ዛቲ ጦማር ዘተፈነወት እምዐበ ብሩ ትበጻሕ ኀበ ክቡር አንጦንዮስ ዘአባዲያ ሰላመ እግዚአብሔር ይኩን ለእ ሌከ አ ክቡር ባርያዎ እርስዎ የሰደዱልኝ ገንዘብ ከፍረጅ (ከፈረንሣይ) (ቆ)ንሱል ከማልጣ ፩፻ ፍራንክ ተቀብዬ በፌ ብሩዋሪ መጨረሻ (፲፰፻፶፰) እስክንድርያ ደረስሁኝ ከዚ ያም የቀረው ፻ ፍራንክ ተቀብየ ወደ ምስር (ካይሮ) መጣ ሁኝ ከዚህም እንሆ ፲ ቀኔ ነው ።

ከማልጣ ሳለሁኝ ሀበሻ ባንድ ንጉሥ (በዐፄ ቴዎድሮስ) ተገዝቶ ጸጥ ብሎ ተቀምጦ ይመስለኝ ነበር ዳሩ ግን ከዚህ

5. ያሰመርኩት እኔ ነኝ የዚህም ትርጉም «ጎንደር ለትምህርት ሄደህ ምን ተምረህ መጣህ» ማለት ይመስላል ።

ጋር መጥቼ ብጠይቅ ሌላ ሆኖ አገኘሁት ፤ አገው ንጉሤ የሚባል ትግሬ ይገዛል ፤ ንጉሡም (ቴዎድሮስ) ጋላው እያሳ መኑ ወታደራቸውም እንዳገራችሁ (እንደ አውሮጳ) አድርጐ ያስተምሩታል ይባላል ። እንደ አውሮጳ ሰው ጥበብ ያወቀ ወደ ንጉሡ የሄደ እንደሆነ አክብሮ ያኖሩታል ይባላል ፤ እኔም ጥበቡ አለመወቄ ናዶኛል ።[6] ወደ ሀበሻ እንዳልወጣም ለመንገድ የሚበቃ ገንዘብ የለኝም ። እግዜር ያመስግንዎ እርስዎ የሰደዱልኝ ከግልጣ አንሥቶ ከዚህ አድርሶ ፲ ብር የሚያህል ቀርቶኛል ፤ የተማሪ ቤት ሰዎችም ለመንገድህ እንካ ይህ ገንዘብ አላሉኝ ወዳጁ (ደ አባድየ) ብዙ ብር ሰዶ ለታል ብሎ ። ስለዚህ ብቻ አይደለም በትሕዛዛቸው ባል ሄድ ነው እንጅ ። ዳሩ ግን አመስግናቸዋ አለሁ እስከ ዛሬ ድረስ አብልቶ አልብሶ አኑረውኛልና ። ለርስዎ እጅግ አጥ ብቄ አመሰግንዎአለሁ ። እርስዎ ገንዘብ ባይሰዱልኝ እኔ እን ደስር ሆኜ እቀመጥ ነው እስከሉቱ ...»

ብሩ ካይሮ በግብጽ ቴሌግራፍ መ/ቤት ተቀጥሮ ሁለት ዓመት (፲፰፻፶፰—፲፰፻፷) ከሠራ በኋላ ፤ ለጥቂት ዓመታት በእንግሊዞች ይካሄድ በነበረው በቀይ ባሕርና በጎንድ የቴ ሌግራፍ ኩባንያ አገልግልዋል ። ከዚህም ወደ ኢትዮጵያ ተመ ልሰው ፤ መኖሪያቸውን በምፅዋና በአካባቢው አድርገው የውጭ ሀገር ልዩ ልዩ ሸቀጦች በተለይም የጦር መሣሪያ ዎች እያስመጡ ለአጼ ቴዎድሮስና ለሌሎቹም የኢትዮጵያ መሳፍንት ይሸጡ ነበር ። በዚህም ምክንያት ዐጼ ቴዎድሮስ ከዚህ የሚከተለውን የንግድ ፈቃድ ሰጥተዋቸዋል ።

«በስመ አብ ወወልደ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ይድረስ በእግዚአብሔር ኃይል ከገዛሁት አገር ሁሉ ብሩን አትንኩት ነግዶ ይብላ ነጣ ብየዋለሁ ።»

በመጨረሻ ግን በድንገተኛ አደጋ ምክንያት ወልቃ ይት ብሩ የሚነግዱባቸው መርከቦች ሁሉ ሰምጠው ፤ ሸቀጣ ሸቀጡ ስለጠፋባቸው ንግዱ እየተዳከመ ሄድዋል ፤ ስለዚ ህም በ፲፰፻፷፯ ዓ. ም. የእንግሊዝ መንግሥት አጼ ቴዎድሮ ስን የሚወጋ ጦር በላከ ጊዜ ብሩ በእንግሊዝ መንግሥት ተቀጥረው ከወታደሮቹ ጋር አብረው ወደ ኢትዮጵያ በመ ሄድ ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ባደረጉት እንቅስቃሴ በልዩ ልዩ

6. ያሰመርኩት እኔ ነኝ ።

ስፍራ ሲረዱ ቆይተዋል ። የእንግሊዝ ወታደሮችም ኢትዮጵያን ከለቀቁ በኋላ (፲፰፻፷፰) ብሩ ጴጥሮስ መቀመጫቸውን በምፅዋ ከተማ አድርገው ፤ ንግዱን ከመቀጠላቸው በላይ ኢትዮጵያ ለመግባት ለሚመጡት አውሮጳውያን ጐብኝዎችና ዲፕሎማቶች በአስተርጓሚነትና በመሪነት ሲያገለግሉ እስከ ሽምግልና ዕድሜያቸው ድረስ ቀይተዋል ። በዚያም ዘመን በምጽዋ ያለፉ አውሮጳውያን በጻፉቸው ጽሑፎች ውስጥ ፤ ስለ ወልቃይት ብሩ (ብሩ ጴጥሮስ) ብዙውን ጊዜ ሳይጠቅሱ አያልፉም ። ወልቃይት ብሩ እንግሊዝኛና/ዐረብኛ ፤ አርመንኛም ጥሩ አርገው ሲያውቁ ፤ በተጨማሪ ትንሽ ትንሽ ፈረንሣይኛ ይነጋገሩ ነበር ። ብሩ ሥራቸውን በአስተርጓሚነት ብቻ ሳይወስኑ ምፅዋ በነበሩበት ጊዜ ለአጼ ዮሐንስ እንደ ፖሊቲካ ኤጀንት ወይም ኢትዮጵያን በምጽዋ በኩል ሊጐዱና ሊወጉ የሚያስቡትን መንግሥታት ቀደም ብሎ የግብጽ መንግሥት (በኋላም የኢጣሊያ መንግሥት) የሚያደርጉትን ንቅናቄና ግንኙነት እየተከታተሉ ለንጉሡ በማቅረብ ምናልባት ለሀገራቸው ጥቅም የፖለቲካ ሰላይ ሆነው ሳይሠሩ የቀረ አይመስልም ። በዚህም ምክንያት በ፲፰፻፸፪ ዓ. ም. በምፅዋ የግብፅ ገዥ የነበረው ሙንዚንገር ወደ ወልቃይት ብሩ ከአጼ ዮሐንስ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በማወቅ ታላቅ ቅጣት አድርሶባቸዋል ። በዚህም ምክንያት አጼ ዮሐንስ ኤደን ለሚገኘው የእንግሊዝ ንግሥት ጉዳይ ፈጻሚ ነገሩን እንዲያውቀው ሙንዚንገርቤይን የሚነቅፍ የወቀሣ ደብዳቤ ጽፈውለታል ፡፡

«... አሁን አንተም የእንግሊዝ ንግሥትም እንድታውቁ የምፈልገው ፤ በምፅዋ የኔ ጉዳይ ፈጻሚ ስለሆነው ስለ ወልቃይት ብሩ ነው ። ሙንዚንገር ጥፋቱን ለኔ ሳይነግረኝ ይዞ ደበደበው ። እንዲህ ያለ ነገር ፤ ያንዱን መንግሥት ቆንስል እየያዙ መደብደብ ፤ በሁሉም መንግሥታት ዘንድ ደንብ ከሆነ ምንም የምናገረው የለኝም... ሆኖም ይህ ክፉ ሥራ በሠሪው ላይ እንደሚወድቅ እርግጥ ነው...»

(ደብዳቤው የተጻፈው እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በጥቅምት ፳ ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. (፲፰፻፸፪ ዓ.ም.) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ሲሆን ከላይ የጠቀስነው ደብዳቤ ከእንግሊዝኛው የተተረጐመ ነው ። ደብዳቤውም የሚገኘው ለንደን «ኢንዲያን ኦፊስ» በተባለው መዝገብ ታሪክ ክፍል ነው)

ስለ ወልቃይት ብሩ የቤተ ሰብ ታሪክ አንዳንድ ማስረጃዎች ለማግኘት ችለናል ። በሰኔ ፯ ፲፰፻፸፮ ዓ.ም. ከጀርመኑ አርቲስት ክሪስቶፍ ኤድዋርድ ዘንደርና ከወይዘሮ ዓመተ ማርያም የሚወለዱትን ወይዘሮ ጥሩነሽን አግብተዋል ። ወልቃይት ብሩም ከወይዘሮ ጥሩነሽ ሶስት ልጆች ወልደዋል ። የነዚህም ስማቸው ፤ ጴጥሮስ ብሩ ጳውሎስ ብሩ እና ሚካኤል ብሩ ነበር ። መንገሻ ብሩ የተወለዱት ወይዘሮ ጥሩነሽን ከማግባታቸው በፊት ነው ።

ወልቃይት ብሩ በ፲፰፻፺፯ ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

<u>ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ፤</u>

ዓለማየሁ ቴዎድሮስ የታላቁ ንጉሥ ቴዎድሮስ ልጅ ነው ። እርሱም እንግሊዞች በ፲፰፻፷ ዓ. ም. ኢትዮጵያን ወግተው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ፤ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ገድለው በመሞታቸው እናትየዋም ወይዘሮ ጥሩወርቅ ወዲያው ታመው በመሞታቸው ልጁን ወደ እንግሊዝ ሀገር ወስዶ ለማስተማር ስለተወሰነ ፤ በዚሁ መሠረት ወደ ለንደን አምርቷል ።

ዓለማየሁም በዚያን ጊዜ የሰባት ወይም የስምንት ዓመት ልጅ ነበር ተብሎ ይገመታል ። በእንግሊዝም ሀገር ካፒቴን ስፒዲ የሚባል ለብዙ ጊዜ በኢትዮጵያ የቆየና የአማርኛ ቋንቋ የሚያውቅ እንግሊዛዊ ሞግዚትና አስተማሪ እንዲሆነው ታዞለት ነበር ። ንግሥት ቪክቶሪያም ፤ ለቴዎድሮስ ልጅ ታላቅ የእናትነት ፍቅር አድሮባቸው ማናቸውም ነገር እንዳይጐድልበት ይከታተሉ እንደ ነበር የገዛ ዳይሪያቸው (ወይም የቀን በቀን ማስታወሻቸው) ለማስረዳት ችሏል።

በ፲፰፻፷፬ ዓ. ም. ካፒቴን ስፒዲ በሥራ ጉዳይ ተቀይሮ ወደ ህንድ ሀገር ከዓለማየሁ ጋር አብሮ ሄዶ ኢትዮጵያዊውን መስፍን እዚያ ት/ቤት አስገብቶታል ። በህንድም እስከ ፲፰፻፷፮ ዓ. ም. ድረስ ቆይቶ ፤ ዓለማየሁ ትምህርቱን ለመቀጠል ወደ እንግሊዝ ሀገር ተመልሷል ። በ፲፰፻፷፯ ዓ.ም. መስፍኑ ከሞግዚቱ ከካፒቴን ስፒዲ ተለያይቶ ጄክስ ብሌክ ከተባለ አስተማሪ ጋር እንዲሆን ተወስኖ እስከ ፲፰፻፷፯ ዓ. ም. ድረስ በዚያ ቆይቷል ። በዚህም ዓ. ም. እንደገና በሊድስ ከሚገኝ ሲሪል ራንሰም ወደ ሚባል ቤት

ሰብ ተዛውሮ እስከ ፲፰፻፸፯ ዓ. ም. ከቆየ በኋላ በመጨረሻም ሳንድ ኸርስት የወታደር ትምህርት ቤት ገብቶ ፤ ይህም ስለአልተስማማው ፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ አቋርጦ ሴሪል ራንስም ወደ ተባለው ቤት ሰብ ተመልሷል ። በዚህን ጊዜ ዓለማየሁ ሀገርና ዘመዶቹ በጣም እንደናፈቁትና ኢትዮጵያም ለመመለስ ደጋግሞ እንደጠየቀ ይነገራል ። ከኢትዮጵያም ስለአለማየሁ ደህንነት ለመከታተል በርቀት ምክንያት አስቸጋሪ ስለነበር የዘመዶቹንና የሌሎቹንም መኳንንት አስተያየት በግልጽ ለማወቅ አልተቻለም ። ሆኖም ከአያቱ ከወይዘሮ ላቂያዬ ለንግሥት ቪክቶሪያ የተጻፈውን የሚከተለውን ደብዳቤ ለማግኘት ችለናል ።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ከወይዘሮ ላቂያዬ የእቴጌ ጥሩ ወርቅ እናት የደጃዝማች ዓለማየሁ እሚታ ፤ የተላከ ይድረስ ለንግሥት እንግሊዝ አንባቢው እጅ ንሣልኝ ። መድኀኔ ዓለም ጤና ይስጥልኝ መንግሥትዎን ያስፉ ጠላትዎን ያጥፉ። ሶስት ደጃዝማች አራተኛው እቴጌ ሙተውብኝ የቀረኝ ደጃዝማች ዓለማየሁ ብቻ ነው ፤ አደራዎን ይጠብቁልኝ እግዚአብሔር አባቱን እናቱን ቢነሣው እርስዎን ስጥቶታል ፤ እኔም ካላየሁት ከሞቱት ቁጥር ነኝ ፤ እርስዎን እናቴ ይላል እንጂ እኔን እናቴ አይለኝም ፤ አላሳደግሁትም ። እርስዎ ያሳደጉት ስለ እግዚአብሔር ብለው ።»

(ይህ ደብዳቤ የተጻፈው በሰኔ ፲፰፻፷ ዓ. ም. ሲሆን የሚገኘውም በለንደን «የኢንዲያን አፊስ» መዝገበ ታሪክ ክፍል ነው)

ሆኖም የእንግሊዝ መንግሥት ዓለማየሁ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ጊዜው ገና መሆኑን በመግለጽ መስፍኑ ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ያቀረበው ጥያቄ ውጤት ሳያገኝ ቀርቷል ። ከዚያም ደስ ሳይለው ሁለት ዓመት ያህል ከኖረ በኋላ ፤ ፕለሪሲ የተባለ በሽታ ይዞት በ፲፱ ዓመቱ በኅዳር ፲ ቀን ፲፰፻፸፱ ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ ።

የእንግሊዝ መንግሥት ስለዓለማየሁ ቴዎድሮስ ምን ዓይነት ዕቅድ እንደነበረው በግልጽ የታወቀ አይደለም ። ሆኖም በእንግሊዝና በአጼ ዮሐንስ የፖለቲካ ግንኙነት አንድ ዓይነት ችግር ተፈጥሮ ቢሆን ፤ ወይም አጼ ዮሐንስ

በድንገት ከዙፋን ቢወርዱና ሀገሪቱ የዙፋን ወራሽ ችግር ቢገጥማት ፤ አንዳንድ ጸሐፊዎች ደጋግመው እንደጠቀሱት ሁሉ ፤ ምናልባት የእንግሊዝ መንግሥት ዓለማየሁን ለማን ገሥ ሳይወስን አይቀርም ነበር ብሎ ለመገመት ይቻላል ። ያም ሆነ ይህ መስፍኑ በሕይወት ሳለም ፤ ከሞተም በኋላ ባለማወቅ ፤ ለብዙ ዓመታት ፤ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ ሀገሩ ተመልሶ ይነግሣል የሚል እምነት በኢትዮጵያ ይወራ ነበር። ይህንንም ወሬ በዚያን ጊዜ ከኢትዮጵያ ጋር ጦር ገጥመው የነበሩ የግብጽ ሹማምንቶች አጼ ዮሐንስን ማስፈራሪያ አድርገውት ነበር ።

## በቅዱስ ክሪሾና ትምህርት ቤት (ስዊዘርላንድ) የተማሩ ኢትዮጵያውያኖች ፤

በቅዱስ ክሪሾና (ስዊዘርላንድ) ፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ ት/ቤት የተላኩት ኢትዮጵያውያን አብዛኛውን ጊዜ የአይሁድን ሃይማኖት የተው ፈላሾች ነበሩ ። በዚህም ት/ቤት ከተማሩት ወጣቶች የታወቁት የደምብያው ሚካኤል አረጋዊ ፤ አጋጀ ሳህሉ ፤ ኃይሉ ወሰን ፤ ጐባው (ወይም ገብሩ) ደስታ ፤ እንግዳሸት እና ሁለቱ ወንድማማቾች ሰማሪ እና ሰምበቱ ዳንኤል ናቸው ። ሚካኤል አረጋዊ ፤ አጋጀ ሳህሉ ፤ ሰመሪ ዳንኤል ፤ ሰምበቱ ዳንኤል እና ኃይሉ ወሰን በ፲፰፻፷ ፲፰፻፷፫ ዓ. ም. በክሪሾና ትምህርት ይከታተሉ እንደነበር ታውቋል ። ሆኖም በ፲፰፻፷፫ ዓ.ም. ኃይሉ ወሰን ከብርድ የተነሣ የሳምባ በሽታ ይዞት ስለሞተ ከእንግዳሸትና ከገብሩ በስተቀር ሌሎቹ በሐኪም ትዕዛዝ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ተደርጓል ። በክሪሾና ከተማሩት ኢትዮጵያውያኖች በጣም የታወቁት ገብሩ ደስታ ነበሩ ።

<u>ገብሩ ደስታ ፤</u>

ገብሩ ደስታም (የቀድሞ ስማቸው ጐባው የነበር) የተወለዱት በ፲፰፻፵፯ ዓ. ም. ግድም አለፋ ጣቁሳ በሚባል አውራጃ ነው ። ምንም እንኳን አንዳንድ ጸሐፊዎች ገብሩ ደስታ ፈላሻ ነበሩ ብለው ቢገምቱም ፤ በዚህ አውራጃ የሚኖሩት ፈላሾች ብቻ አልነበሩም ። ገብሩ ከአለፋ ጣቁሳ ለቀው ከዘመዶቻቸው ጋር ወደ ደምቢያ ሄደው ከዚያም ገና በሕፃንነታቸው የአጼ ቴዎድሮስ ዋና ከተማ ወደ ነበረው

ወደ ደብረ ታቦር ሄደው ዋልደሜር ከተባለው ፕሮቴስታ ንት ሚሲዮናዊ ጋር ተዋውቀው ከሱ ጋር ተቀምጠው ይማሩ ጀመር ። ከመቅደላም ጦርነት በኋላ ፤ ከቴዎድሮስ ጋር ቆይተው የነበሩት አውሮጳውያን ፕሮቴስታንት ሚሲዮ ናውያን ኢትዮጵያን ለቀው በሄዱ ጊዜ ፤ ገብሩ ከዋልደሜር ጋር አብረው ሄደው በኢየሩሳሌም የፕሮቴስታንት ት/ቤት ገብተው ሲማሩ ቆይተዋል ። በ፲፰፻፸፯ ዓ. ም. በቲኦሎጂ (የሃይማኖት ትምህርት) ዲፕሎማ ተመርቀው ፤ ከ፲፰፻፸፯ -፸፱ ዓ.ም. ወደ ቩርተንበርግ (ጀርመን) ሄደው ኢትዮጵያ ብዙ ዓመት ተቀምጦ የነበረውን ጀርመናዊው ፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊ ዶክተር ክራፕፍ ፤ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማ ርኛ ለመተርጎም ረድተውታል ። በመጨረሻም በ፲፰፻፸፱ ዓ. ም. ሚሲዮናውያን አስተማሪዎች ገብሩ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ፈላሾችን የክርስቲያን ሃይማኖት እንዲያስተምሩ ወስነው ወደ ኢትዮጵያ ልከዋቸዋል ።

ገብሩ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኋላ በተከታታይ በደ ምቢያ (ፈላሾች) በጉድሩ (ሲጋሎች) እንዲሁም በባሌ የሚ ሲዮን ት/ብቶችን ከፍተው ለጥቂት ጊዜ በሦስቱም ሥፍ ራዎች ሲያስተምሩ ቆይተዋል ።

በ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. አጼ ዮሐንስ አውሮጳውያን ሚሲ ዮናውያንን (ካቶሊክና ፕሮቴስታንት) ከኢትዮጵያ ሲያስ ወጡ ፤ ገብሩም አብሮ ተከትሎዋቸው ወጥተው በኢየሩሳ ሌም በሶሪያና በዳሬሰላም እንደዚሁም በኤደን የፕሮቴስታንት ሚሲዮን ት/ቤት ተልከው ሲያስተምሩ ቀይተዋል ። ከዚ ያም እንደገና በ፲፰፻፹፱ ዓ. ም. ኢትዮጵያ ተመልሰው ፤ የሃይማኖት አስተማሪነቱን ትተው በልዩ ልዩ የፖለቲካ ደረጃ ሀገሩን አገልግለዋል ።

በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም. ልዑል ራስ መኰንን ወደ ኢየሩሳ ሌም የኢትዮጵያ መልክተኛ አድርገው ልከዋቸዋል ።

ከአድዋ ጦርነት በኋላ (፲፰፻፺፪) አጼ ምኒልክ የጐን ደር ከንቲባ አገርው ሾመዋቸዋል ።

በ፲፰፻፺፯ ዓ. ም. በሱዳንና በኢትዮጵያ መሃል ስላለው የፖለቲካ ግንኙነት ለመነጋገር ወደ ኡምዱርማን ተልከዋል ።

በ፲፱፻፭ ዓ. ም. ከልዑል ራስ መኰንን ጋር ለንደን አብረው ሄደዋል

ሆኖም ገብሩ በቀድሞ ሃይማኖታቸው ምክንያት (በፕሮቴስታንት) ከአዲስ አበባ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እንዲሁም የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ዋና ተቆርቋሪ ነን የሚሉት መሳፍንትና መኳንንት ተቃዋሚዎች ነበሩ ቸው ። ከነዚህም ዋናቹ አቡነ ማቴዎስና እቴጌ ጣይቱ ራሳ ቸው ነበሩ ። በዚህም ምክንያት አልፎ አልፎ ገብሩ ደስታ እሥር አልቀረላቸውም ነበር ። ከፍተኛም ሹመት እንዳያ ገኙ ፤ ሀብታቸው ርስትና ንብረታቸውም በጣም አነስተኛ እንዲሆን ምክንያት የሆነው ይህ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ይገመታል ። አጼ ምኒልክም ከአረፉ በኋላና ፤ እቴጌ ጣይቱ ከሥልጣን ከለቀቁ ወዲህ ልጅ ኢያሱ ከንቲባ ገብሩን የን ጉሥ ሚካኤል አማካሪ እንዲሆኑ ደሴ ልከዋቸው ነበር ። ግን ልጅ ኢያሱ በ፲፱፻፰(፲፱፻፲፮) ዓ. ም. ከዙፋን ሲወር ዱና ፤ ንግሥት ዘውዲቱ ሲነግሡ ከንቲባ ገብሩ በእስር እን ዲቀመጡ ሆኑ ። በዚህም ጊዜ የሚከተለውን ግጥም ጽፈ ዋል ።

እርሻዋም ዓለም መውደድ ናት
በአጼ ቴዎድሮስ ዘመነ ሁከት ፤
ጣቁሳ ላይ ሆኖ የተወለድኩት ፤
በሰኔ ፲፰፻፵፰ ዓመተ ምሕረት ፤
እንደ ፍቅር ሁሉ ዕጣዬ ሆኖ ስደት
ሳለኝ ብዙ ርስት በየሄድኩበት
ለኔ የሚበቃኝ ሶስት ክንድ መሬት ፤
ሄጄ ለመጠበስ እንደ እሳት እራት ፤
እርቦኝ እዞራለሁ በቃኝ አለማለት ፤
በአራት ነሐሴ ፲፱፻፱ ዐመተ ምሕረት
ተጻፈ በዘውዲቱ ምኒልክ መንግሥት ።

(ስለ ከንቲባ ገብሩ ፤ በባይሩ ታፍላ የተጻፈውን ጽሑፍ ተመልከት ፤ ጆርናል ኦፍ ኢትዮጵያን ስተዲስ ፤ ቮልዩም ቁጥር ፪ ፤ ፲፱፻፷፱ ዓ. ም.)

ይህም ቢሆን በ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. እንደገና ከብላታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ጋር ወደ እንግሊዝ አገር ተልከው ሄደው ነበር ። ቀጥሎም በ፲፱፻፴፩ ፓርላማ ሲቋቋም ፤ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆነው ተሹመዋል ።

ጣሊያንም ኢትዮጵያን በያዘ ጊዜ አዚናራና በኋላም ሜር ኮሊያኖ (ኔፕልስ) ውስጥ ታስረው ቆይተው በ፲፱፻፴ ዓ. ም.

በሕመም ምክንያት ጣሊያኖች ኢትዮጵያ መልሰዋቸው ነበር ። ከነፃነትም በኋላ እንደገና በፓርላማ ዓባልነት መሥራት ቀጥለው በጥር ፲፱፻፶ ዓ.ም. ከዚህ ዓለም አልፈዋል ።

ከንቲባ ገብሩ ትልቅ ቤተ ሰብ ትተው ሄደዋል ። ከንቲባው በመጀመሪያ ጊዜ የታጩት በ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. ገደማ ለፕሮቴስታንት አስተማሪያቸው ለጆን ሜየር ልጅ ነበር ፤ ሆኖም ይህ ሳይሳካ ቀርቶ በ፲፰፻፹፱ ዓ. ም. ማርታ ቤንደር የተባለችውን የሌላ ሚሲዮናዊ ልጅ አግብተው ፤ ይህም ጋብቻ ፍሬ ሳይሰጥ ባለቤታቸው ሐረር ውስጥ በዚሁ ዓመት በበሽታ ምክንያት አረፉ ። ከዚያም ከንቲባ ገብሩ ከልዩ ልዩ ጋብቻ ፤ ወይዘሮ ስንዱ ገብሩን ፤ ወይዘሮ ደስታ ገብሩን ፤ ወይዘሮ ብርሃኔ ገብሩን ፤ እማሆይ ጽጌረዳ ገብሩን ፤ ኮሎኔል ዳዊት ገብሩን ወልደዋል ።

## ሃኪም ወርቅነህ እሸቱ (ዶክተር ቻርልስ ማርቲን) ፤

በቀድሞ ዘመን ውጭ ሀገር ከተማሩት ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ትምህርት ያገኙና ከሁሉም የበለጠ ደረጃ የደረሱ ወርቅነህ እሸቱ ነበሩ ።

ወርቅነህ ትውልዳቸው ጐንደር ሲሆን የተወለዱት በጥቅምት ፲፰፻፷፫ ዓ. ም. ነው ። እንግሊዞች በአፄ ቴዎድሮስ ላይ ባደረጉት የመቅደላ ጦርነት (፲፰፻፷፯—፷፰) ጊዜ ወርቅነህ የአራት ዓመት ልጅ ሳለ የእንግሊዝ ጦር ሲመጣ ዘመዶቹ ጥለውት ስለሸሹ ፤ ሕፃኑ እናት አባት የለውም ብለው በመገመት ወታደሮች አንሥተው ፤ ከጦርነቱም በኋላ ቻርልስ ቻምበርሌን ከሚባል የጦር መኰንን ጋር አብሮ ወደ ህንድ ሀገር ሄድዋል ። ቻርልስ የሚባለውንም ስም ወርቅነህ የወሰደው ከዚሁ ከአሳደገው የጦር መኰንን ነው ። ሆኖም ቻርልስ ቻምበርሌን ሕፃኑ ገና ሰባት ዓመት እንደሆነው ማለት በ፲፰፻፸፩ ዓ. ም. ስለሞተ ወርቅነህ ወደ ፑንጃብ (ህንድ) የሚሲዮን ት/ቤት ተልኮ ሚሲዮናውያኖች አሳዳጊ አባት እንዲሆነው ኮሎኔል ማርቲን ለሚባል እንግሊዛዊ መኰንን ሰጥተውታል ። ወርቅነህ ማርቲን የተሰኘውን ሁለተኛውን ስሙን ያገኘው ከዚሁ ኰሎኔል ማርቲን ከተባለው የእንግሊዝ ተወላጅ ነው ።

በ፲፰፻፸፺ ዓ. ም. ቻርልስ ማርቲን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ፈጽሞ ላህር የሕክምና ኰሌጅ ገብቶ ከዚያም

በጠቅላላ ሕክምናና በሰርጀሪ ዲፕሎም አግኝቶ በ፲፰፻፹፪ ዓ. ም. ተመርቆአል ። በዚያን ጊዜም ፳፪ ዓመቱ ነበር ። ትምህርቱንም እንደጨረሰ በሰርጀንነት ተቀጥሮ ሰባት ዓመት ካገለገለ በኋላ በ፲፰፻፹፱ ዓ.ም. ወደ እንግሊዝ አገር ሄደ ። እዚያም በግላስጎና በኤደንበርግ ከፍተኛ የሕክምና ጥናት ከአደረገና ከተመረቀ በኋላ በ፲፰፻፺—፩ ዓ. ም. ወደ ህንድ አገር ተመልሶ በልዩ ልዩ ሥፍራ ሲያገለግል ቆይቷል ።

በ፲፰፻፺፰ ዓ. ም. ጣሊያን በኢትዮጵያ ላይ ጦርነት እንዳደረገ በሰማ ጊዜ አገሩ ለመመለስ ቆርጦ ኤደን መጥቶ ነበር ። ነገር ግን ወደ አዲስ አበባ ለመኻዝ የማለፊያ ፈቃድ በመከልከሉ ወደ ህንድ አገር ተመልሷል ። የዚህም ወሬ አፄ ምኒልክ ዘንድ ደርሶ ፤ በርሳቸው ጠያቂነት ሀኪም ወርቅነህ በ፲፰፻፺፱ ዓ. ም. አዲስ አበባ ለመምጣት ችሏል ። የሀገሩንም ቋንቋ ስለረሳ የሚነጋገረው በአስተርጓሚ ነበር ። ወርቅነህ አዲስ አበባ በቆየበት ጊዜ ምንም እንኳን አንዳንድ ዘመዶቹን ለማግኘት ቢችልም እናቱ ወይዘሮ ደስታ ወልደማርያምና አባቱ ነጋድራስ እሸቱ ወልደማርያም ከሞቱ ብዙ ጊዜ እንደሆነው ተረድቷል ። ዶክተር ቻርልስ ወርቅነህ እስከ ፲፱፻፪ ዓ.ም. ድረስ ኢትዮጵያ ከቆየ በኋላ ትምህርት ቤት ለማስገባት አምስት ልጆች ይዞ ወደ በርማ ተመልሷል። ሆኖም ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና የእንግሊዝ ሌጋሲዮን ሃኪም ሆኖ አዲስ አበባ ተመልሶ አምስት ዓመት ቆይቷል። ለአፄ ምኒልክም በመጨረሻ ከደረሰባቸው ሕመም ሕክምና ከሚያደርጉላቸው ዶክተሮች አንዱ ነበር ። በ፲፱፻፲፫ ዓ. ም. ማርቲን እንደገና ወደ በርማ ተመልሶ እስከ ፲፱፻፲፱ ዓ. ም. ከቆየ በኋላ በዚሁ ዓመተ ምኅረት ከህንድ የእንግሊዝ መንግሥት የመጨረሻ ስንብት ወስዶ ኢትዮጵያ ሀገሩ መጥቶ እስከ ዕድሜ ልኩ ለመኖር ወስኖአል ።

ኢትዮጵያ ከተመለሱ ጀምሮ ፤ ሃኪም ወርቅነህ ከያዟቸው ሥራዎች ዋና ዋናዎቹ ፤

— በ፲፱፻፳፭ ዓ. ም. የተፈሪ መኰንን ት/ቤት ሲከፈት ዋና ዲሬክተር ሆነዋል ።

— በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም. ወደ አሜሪካን መንግሥት ስለ ጣና ግድብ ለመነጋገር ተልከው ነበር ።

— በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. የውጭ ሀገር ሰዎች ጉዳይ ዳኛ ሆነዋል ።

— በ፲፱፻፴ ዓ. ም. ጨርጨርን ገዥነት ተሾሙ ።
— በ፲፱፻፴፫ ዓ. ም. ዳናክልን ገዥነት ተሾሙ ።
— በ፲፱፻፴፮ ዓ. ም. በእንግሊዝ የኢትዮጵያ አምባ ሳደር ሆነው ተሾሙ ።

ከዚህም በላይ ዶክተር ማርቲን ቻርለስ ወርቅነህ የልዩ ልዩ ጽሑፎች ደራሲ መሆናቸው ሲታወቅ ፤ ከእነዚህም አንዱ በ፲፱፻፳፯—፳፰ ዓ. ም. በአማርኛ ያሳተሙት «የዓለም ጂኦግራፊ» ነው ።

ዶክተር ቻርለስ ማርቲን ወርቅነህ በ፲፱፻፵፬ ዓ. ም. በአዲስ አበባ አርፈዋል ።[7] እርሳቸውም ከወይዘሮ ቀጸላ ወርቅ ቱሉ ፲፫ ልጆች ወልደዋል ።

## በስዊድን ዮሐንንሎንድ ሚሲዮን ኢንስቲቱት የተማሩ ኢትዮጵያውያን ፤

ከ፲፰፻፸፯ ዓ.ም. ጀምሮ ስቶክሆልም አካባቢ በሚገኘው ዮሐንንሎንድ ተብሎ በሚጠራው የስዊድን ፕሮቴስታንት ሚሲዮን ትምህርት ቤት ፤ ኢትዮጵያ በተቋቋመው የሚሲዮኑ ቅርንጫፍ አማካይነት አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ተልከው ነበር ። ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ።

### <u>ኦኔሲሞስ ነሲብ ፤</u>

ኦኔሲሞስ ነሲብ የወለጋ ጋላ ሲሆን የተወለደው በ፲፰፻፶፱—፷ ዓ. ም. ሁሩሙ ተብሎ በሚጠራ ዛሬ በኢሉባቦር ግዛት ውስጥ በሚገኝ ቀበሌ ነው ። ከዚያም በልጅነቱ ከብት ሲጠብቅ በባርያ ነጋዴዎች ተዘርፎ ከአንድ ሻጭ እጅ ወደ ሌላ ሲተላለፍ ቆይቶ በመጨረሻ ምፅዋ ሲደርስ ፤ ሙንዚንገር የተባለው የፈረንሣይ ቆንስል ነፃ አውጥቶት ስዊድኖች ወደሚያካሄዱት ትምህርት ቤት ልኮታል ። በዚያም ጊዜ ስሙ ነሲብ ነበር ። በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም. ክርስቲያን ሲሆንም ኦኔሲሞስ ተባለ ። በዚህም ትምህርት ቤት ለጥቂት ዓመታት ከቆየ በኋላ የትምህርት ቤቱ

---

7. ስለ ሃኪም ወርቅነህ የሪቻርድ ፓንክረስት ጽሑፍ <u>ኢትዮጵያ ኦብዘርቨር</u> ቮልዩም ስድስት ቁጥር ፫ ተመልከት ።

አላፊዎች በሰኔ ፲፰፻፷፰ ዓ.ም. ወደ ዮሐንንሉንድ ኢንስቲቱት (ስዊድን) ልከውታል ። ከዚያም እስከ ፲፰፻፸፫ ዓ.ም. ድረስ ሲማር ከቆየ በኋላ በመጨረሻ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል ።

ኢትዮጵያም ከተመለሰ በኋላ ኦኔሲሞስ በስዊድን ሚሲዮን ሥራ በጋልኛ ልዩ ልዩ የሃይማኖት ጽሑፎች በማቅረብና እንዲሁም ከሌሎች ቋንቋዎች ወደ ጋልኛ በመተርጐም አገልግሏል ። ከሥራ ውጤቶቹም ታላቅና በጉልህ የሚታየው ኦኔሲሞስ የተረጐመው የጋልኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው ።

ከዚህም በኋላ ኦኔሲሞስ ወደ ወለጋ ሄዶ እስከ ሕይወቱ መጨረሻ ድረስ ሲሰብክ ቆይቷል። በየጊዜውም በሃይማኖቱ ምክንያት ፤ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ቀሳውስት ተቃውሞ ልዩ ልዩ ችግር ደርሶበት ነበር ።

ኦኔሲሞስ ሰኔ ፲፱፻፳፫ ዓ. ም. ከዚህ ዓለም ተለይቷል ።

<u>ኃይለ ሚካኤል ኪዳኔ</u> ፤ (፲፰፻፸—፲፱፻፵፫) ምንኩሉ በሚገኘው የስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ከቆየ በኋላ በ፲፰፻፹ ዓ. ም. ወደ ስዊድን ተልኳል ። ከዚያም እስከ ፲፰፻፹፯ ዓ.ም. ትምህርቱን በመከታተል ከቆየ በኋላ ኢትዮጵያ ተመልሶ በስዊድን ሚሲዮን ት/ቤት በአስተማሪነት ሲያገለግል ቆይቷል ።

<u>ተወልደ መድኅን ገብረ መድኅን</u> ፤ (፲፰፻፸—፲፱፻፵፬) የሃማሴን ተወላጅ የሆኑ ስዊድን በ፲፰፻፹፫ ዓ. ም. ሄደው እስከ ፲፰፻፹፯ ዓ. ም. ድረስ ቆይተዋል ። ወደ ኢትዮጵያም ተመልሰው በምንክሉ በገለብ በመንሳ እንዲሁም በሌሎች ሥፍራዎች ሲያስተምሩ ቆይተዋል ። ከዚህም ሌላ በትርጉም ሥራ ሚሲዮኑን ሲያገለግሉ ቆይተዋል ።

<u>ማርቆስ ግርማይ</u> ፤ (፲፰፻፸፪—፲፱፻፵፩) በስዊድን ከ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. እስከ ፲፰፻፹፱ ዓ. ም. ድረስ ቆይተዋል ። ወደ ኢትዮጵያም ተመልሰው በማስተማርና ከትግርኛ በመተርጐም ረድተዋል ። ማርቆስ ግርማይ በ፲፰፻፺፱ ዓ.ም. ሬጅና ዮሐንስን የተባሉ የስዊድን ተወላጅ አግብተው በመጨረሻም በ፲፱፻፵፪ ዓ. ም. ወደ ስዊድን ተመልሰው እዚያው ሳሉ በ፲፱፻፵፩ አርፈዋል ።

ናትናኤል ሀገና ፤

የኩናማ ተወላጅ ሲሆን ከባርያ ሻጭዎች ነፃ ወጥቶ በምጽዋ የስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብቶ በ፲፰፻፸፪ ዓ. ም. በክርስትና ተጠምቋል ። ከዚያም በ፲፰፻፹፩ ዓ. ም. ወደ ስዊድን ለትምህርት ሄዶ እዚያው ሳለ በ፲፰፻፹፫ ዓ. ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል ።

ከዚህ በላይ ያየነው ከ፲፰፻፹፱ ዓ. ም. በፊት በውጭ አገር የተማሩትን ኢትዮጵያውያን አጭር ታሪክ ነው ። ፲፰፻፹፱ ዓ. ም. አፄ ዮሐንስ የሞቱበት ሲሆን ፤ ከዚያም በኋላ አፄ ምኒልክ ነግሠው ፤ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ወደ አዲስ አበባ (ሸዋ) ተዛውሯል ። ጥናታችንንም በዚህ ዓመተ ምሕረት ያቆምነው ከአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በኋላ ውጭ አገር የተማሩት ተማሪዎች አቋም ፤ ማለት ወደ ውጭ ለመሄድ ምክንያት የሆናቸው ፤ በውጭ የተማሩት ትምህርት፤ ሲመለሱ የያዙት ሥራ ወይም ሹመት ከቀድሞዎቹ ለየት ያለ ስለሆነ ነው ።

ከ፲፰፻፹፱ ዓ. ም. በፊት በውጭ ሀገር ሄደው የተማሩት ኢትዮጵያዊያን አብዛኛውን ጊዜ የተላኩት በአውሮጳውያን ሚሲዮናውያን አማካይነት ሲሆን ፤ የተከታተሉትም ትምህርት ከጥቂቶቹ በስተቀር የሃይማኖትና የቋንቋ ልምምድ ነው ። ይህም ስለሆነ አብዛኛዎቹ ሀገራቸው ተመልሰው የነበራ ቸው ተግባር ሃይማኖት አስተማሪነትና ሰባኪነት ወይም ደግሞ አስተርጓሚነት ነበር ።

በተመለከትናቸው ዘመናት ውስጥ የአስተርጓሚዎች ቦታ ከፍተኛ ኃላፊነት ያለው ነበር ። የውጭ ሀገር መን ግሥት ወደ ኢትዮጵያ የሚልኳቸው ደብዳቤዎች የሚተረ ጐሙት በእነዚህ በውጭ ሀገር ተምረው በመጡ ተማሪዎች ሲሆን ፤ ደብዳቤውን ጥሩ ወይም መጥፎ አድርጎ በመተርጐም የንጉሡ ነገሥቱን ወዳጅነት ወይም ጠላትነት ለማፍራት ይቻላል ። ሁለተኛም የውጭ ሀገር ዲፕሎማቶች ፤ መልክ ተኞቹ ወይም ሀገር ተመልካቾች ኢትዮጵያ መጥተው ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ቀርበው የመጡበትን ጉዳይ ጥሩ ፍጻሜ ለማድረስ የአስተርጓሚው መልካም ፈቃድና ችሎታ ከመ ጀመሪያዎቹ ተፈላጊ ነገሮች አንዱ ነበር ። የግራዝማች

ዮሴፍ[8] የውጫሌ ስምምነት ትርጉም የአድዋ ጦርነት አማካይ ምክንያት እንደነበር ለሚያውቅ ሁሉ በዚያን ዘመን ስለነበሩ አስተርጓሚዎች ታላቅ ኃላፊነት መረዳት ቀላል ነው ። ከውጭም ሆነው እንደ ወልቃይት ብሩ በሞፅዋ ፤ ለአውሮጳውያን በአስተርጓሚነት ይሠሩ የነበሩት ወጣቶች ፤ ስለ አውሮጳውያንና ስለ ሌሎችም ሀገሮች መንግሥታት በኢትዮጵያ ላይ የሚያቅዱትን የጦር ወይም የፖለቲካ ምስጢር ለንጉሠ ነገሥቱ በመጻፍና በመንገር ሀገራቸውን ረድተዋል ። በዚህ ዓይነት ታላቅ ዕርዳታ የሰጠውና ሀገሩን በከፍተኛ ደረጃ የጠቀመው ጴጥሮስ ጊዮርጊስ መታወስ አለበት ። ጴጥሮስ የተማረው በካይሮና ምናልባትም በኢየሩሳሌም ሲሆን ፤ የቋንቋ ችሎታው ዐረብኛና ጥቂት እንግሊዝኛ ነበር ። በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. ጣሊያኖች ምጽዋንና ሌሎችንም የባሕር አዋሳኝ የሆነውን የኢትዮጵያ መሬት ከያዙ በኋላ አጼ ዮሐንስ ጣሊያንን ለመግፋት ጦራቸውን በሚያሰናዱበት ጊዜ ጣሊያኖች ጴጥሮስ ጊዮርጊስን ከካይሮ አስመጥተው አስተርጓሚ አድርገውት ስለነበር ፤ ጴጥሮስ ጣሊያኖች በእንግሊዞች ዕርዳታ የኢትዮጵያን መሬት ለመያዝ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በሙሉ በየጊዜው በጽሑፍ ለራስ አሉላና ለንጉሡ ያስተላልፍ ነበር ። ይህም በመጨረሻ በጣሊያኖች ታውቆ ጴጥሮስ ታስሮ ከሥራ ተወግዶአል ። አስተርጓሚዎች በዚህ ዘመን ሥራቸው ማስተርጐም ብቻ አልነበረም ። በንጉሠ ነገሥቱ የተመረጡት አስተርጓሚዎች እንደ ምርጫ ወርቂ ወይም እንደ ማኅደረ ቃል ያሉት በጠቅላላው ከአውሮጳና ከውጭ ነገሥታት ጋር ኢትዮጵያ ስለ ምታደርገው ግንኙነት እንደ አማካሪ ሆነው ይሠሩ ነበር ። ይህም ስለሆነ እነዚህ አስተርጓሚዎች ምርጫና ማኅደረ ቃል እንዲሁም ግራዝማች ዮሴፍ ከውጭ ሀገር ተወላጅ ጋር በነበራቸው ግንኙነት አንዳንድ ጊዜ በውጭ አገር ጋዜጦች ውስጥ በሚያወጧቸው ጽሑፍ ውስጥ ራሳቸውን የሚያስተዋወቁት «የኢትዮጵያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር» በማለት ነበር ።

8. በዚህ ጥናት ውስጥ ያላስገባናቸው ፤ በትግሬ የላዛሪስት ሚሲዮን ተማሪ መሆናቸውን ስናውቅ ውጭ ሀገር ሄደው ይማሩ አይማሩ ለማወቅ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስላላገኘን ነው ።

ነገር ግን ካየናቸው ውጭ አገር ተምረው ከተመለሱት ወጣቶች ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ በንጉሠ ነገሥቱ ምንም ዓይነት የሹመት ስም አልተሰጣቸውም ነበር ። እንዲያውም ብዙውን ጊዜ እስከነ «አቶ»ውም ተነሥተው የሚጠሩት በስማቸው ነበር ። ኋላ በሸዋ ለአንዳንድ ለተማሩ ሰዎች ይሰጥ የጀመረው «ብላታ» ወይም «ብላቴን ጌታ» የተባለው ሹመትም እስካሁን ላየናቸው ተማሪዎች ለአንዳቸውም አልተሰጠም ነበር ።

ይህ ለምን ሆነ ብለን የጠየቅን እንደሆነ አንድ ሁለት መልሶች እናገኛለን ። መጀመሪያ ደጋግመን እንዳየነው እነዚህ ውጭ የተማሩት ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ ከመሄዳቸው በፊት ወይም ሲመለሱ ሃይማኖታቸውን ስለሚለውጡ፤ ማለት ካቶሊክ ወይም ፕሮቴስታንት ሆነው ስለሚመለሱ፤ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በጣም ጠንካራ በሆነበት በኢትዮጵያ ውስጥ እጅግም ተቀባይነት አልነበራቸውም ። ፕሮቴስታንቱ ፀረ ማርያም ተብሎ የሚጠራበት ፤ ካቶሊኩ ከክርስቲያኖች ጋር ሳይሆን ከእስላሞች ጋር የሚቆጠርበት ዘመን ነበር ። ነገሥታቱና መኳንንቱም ከውጭ የተመለሱትን ኢትዮጵያውያን ከሹመትና ከታላቅ ደረጃ ያላደረሷቸው አንዱ ምክንያት ይህ ሊሆን ይችላል ።

ሌላው ምክንያት ደግሞ እነዚህ ወጣቶች ከውጭ ሲመለሱ ይዘው የሚመጡት የውጭ ሀገር አለባበስ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የባህል ለውጥ ነው ። በ፲፰፻፵፩ ዓ. ም. አንድ ገብረ ማርያም የሚባል ወጣት ደጃኮቢስ ከሚባለው የካቶሊክ ሚሲዮናውያን አለቃ ጋር አውሮጳ ደርሶ ሲመለስ በዚያን ጊዜ ትግሬን ይገዛ ከነበረው መስፍን ከደጃች ውቤ ፊት ቀርቦ «ኢትዮጵያ የምትገዛው በደደቦች ነው ። ኢትዮጵያ ጨለማ ስትሆን አውሮጳ ብርሃን ነው ፤» በሚል መልክ ትልቅ ዲስኩር አሰምቶ ውጤቱ አርባ ጅራፍ እንደነበር ለፌቭር የተባለው ፈረንሣዊ አስታውሷል ። እንዲሁም በጠቅላላው ሲነገር ውጭ ተምረው የሚመለሱት ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳን እንደ ገብረ ማርያም ደፍረው ባይናገሩም ፤ ለአውሮጳውያን ጉብኝዎች ስለ ኢትዮጵያ ወደ ኋላ መቅረትና ወደ ፊት መሻሻል በሰፊው ያጫውቷቸው ነበር ። ሆኖም በዚያ ዘመን የነዚህ ልጆች ቁጥር በኢትዮጵያ ውስጥ ውቅያኖስ ውስጥ እንደተወረወረ ፍንጣቂ ስለነበር ፤ ቀን ፤ ወር ፤ ዓመት እንዲሁም ዓመታት ሲያልፉ ፤ ለውጥ ማም

ጣት የፈለጉት ወጣቶች ራሳቸው ተለውጠው እንደ ዘመኑ ጥሩ ኢትዮጵያዊ መስለው ይኖሩ ነበር ። አንዳንድ አውሮጳውያን ሲጽፉ ውጭ ሀገር ብዙ ዓመታት ተምረው የመጡት ኢትዮጵያውያን ሀገራቸው ተመልሰው ጥቂት ከቆዩ በኋላ ፤ ያ ሁሉ ለኢትዮጵያ ለውጥ ከአውሮጳ ያመጡት ሃሳብ ተረስቶ ፤ የቀራቸው ከውጭ የተማሩት ቋንቋ ብቻ ነበር እያሉ ጽፈዋል ። ኢትዮጵያ ሲመለሱም የነበራቸው የአለባበስ ለውጥ ፤ ከሕዝቡ ሊያርቃቸው ይችል ይሆናል ። እንደ አውሮጳውያን ኮት ሸሚዝና ሱሪ በተለይም ጫማ በማይደረግበት በዚያ ዘመን ፤ ውጭ ሀገር የተማሩትን ልጆች መለያ ፤ በአለባበሳቸው ነበር ። (እቤታቸው ሲኬድ አንዳንዶቹ በማንኪያና በሹካ እንደሚበሉ ፤ የሚጠጡት በዋንጫ መሆኑ ቀርቶ በብርጭቆ ጠላና ጠጅ መሆኑ ቀርቶ አረቄና አንዳንድ ጊዜም ዊስኪ እንደነበር ተጽፏል) ። እንደዚህም ያለው የአለባበስና የሌላም የሀገር ልማድ ለውጥ በጣም የተወደደ እንዳልነበረ መገመት ይቻላል ። ይህንንም ለመረዳት አንድ አውሮጳዊ ጸሐፊ ሲጽፍ ሁለት ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ከውጭ ሲመለሱ አጼ ዮሐንስ ፊት ከነጫማቸው ቀርበው በዚሁ ምክንያት ንጉሡ በንዴት «ኢትዮጵያ ውስጥ ጫማ አናደርግም የምንሄደው በእግራችን ነው» ብለው እንዲወጡ አዘዋቸዋል ብሏል ። ምንም እንኳን ይህ የተነገረው እውነተኛ ሊሆን ባይችልም ፤ የውጭውን ባህል ቀድተው በሚመጡት ልጆች ላይ የነበረውን ተቃውሞ ሊያስረዳ ይችላል ። ሆኖም እንደሌላው ሁሉ የአለባበሱም ለውጥ በብዙ ጊዜ አይቆይም ። ከአውሮጳ ርቀት የተነሣ ተማሪዎቹ ይዘው የተመለሱት ልብስና ጫማ እስኪያልቅና ተቀዳዶ እስከሚለጣጠፍ ድረስ ይለበስና ፤ በኋላ እንደ ገና ወደ እጀጠባብ መመለሱ ግድ ነበር ። አንዳንድ አውሮጳውያን በአለቀ ጫማና በአለቀ የአውሮጳ ልብስ ስለሚያጋጥሟቸው ውጭ ተምረው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ዘርዝረው በጽሑፍ የሳሉትን ማንበብ አስቂኝና አሳዛኝ ነው ።

ጥናታችንንም ለመደምደም ያህል ፤ ውጭ ሀገር ተምረው የሚመለሱት ተማሪዎች በሚታይባቸው ጠቅላላ የባህልና የአስተያየት ለውጥም ሆነ ፤ ወይም በተለይ የውጭ ሀገር ሃይማኖት በመከተላቸውና የውጭ ሀገር ቋንቋ በመነጋገራቸው ፤ ከማኅበራዊ ኑሮ የራቁና በጥርጣሬ የሚታዩ ነበሩ ቢባል ብዙ እውነት ያዘለ ሳይሆን አይቀርም ። ይህንንም ለመረዳት የሚከተለውን ከገብረ ሕይወት ባይከዳኝ

«አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» ከተባለው ጽሑፍ የወሰድነውን መመልከት ነው ።

«እስከ ዛሬ ድረስ ሳይወዱ ሩቅ አገር ተሰደው ወይም ወደ አበሻችን ከሚመጡ ፈረንጆች ጥቂት ጥበብ ተምረው ያገራቸውን መንግሥት ሊጠቅሙ የሚፈልጉ ወንድሞቻችን ፕሮቴስታንት ፤ ካቶሊክም መናፍቃን የሌላ መንግሥትም ሰላዮች እየተባሉ ሲራቡ ሲከሰሱም እናይ የለምን ። የነዚያን መከረኞች ስም ስንት ብለን እንቁጠር ። የሚከተሉት የሁለት ሰዎች ስም ግን እንዲወሱ የግድ ነው ። እነሱም ከንቲባ ገብሩና አለቃ ታዬ ናቸው ። ሶስት ዓመት ሙሉ አዲስ አበባ ላይ ስቀመጥ እንደ እነዚህ ሰዎች አድርጐ መንግሥቱን የሚወድ አላየሁም ። ይህ ደግነታቸው ግን እስከ ዛሬ ድረስ አልታወቀላቸውም ይመስለኛል ። እጅግ ያሳዝናል ። የነሱን ዕድል ያየ ሰው የኢትዮጵያ መንግሥት ለወዳጁ አይጠቅምም ብሎ ተስፋ ይቆርጣልና ።»

ይህንንም የመሰለው አስተያየት ለጥናታችን ከወሰነው ዘመን አልፎ በሃያኛው ክፍለ ዘመን የቀጠለ ለመሆኑ የሚከተለው «ብርሃንና ሰላም» ተብሎ ይጠራ በነበረው ጋዜጣ ላይ ጥር ፲፬ ቀን ፲፱፻፲፯ (፲፱፻፳፭ እ. ኤ. አ.) ሰፍሮ የሚገኘው ጽሑፍ ሊያስረዳን ይችላል ። ይህም ጽሑፍ የተዘጋጀው በዚያው ጊዜ ይታተም በነበረው በሁለተኛው የአማርኛ ጋዜጣ አእምሮ ውስጥ ውጭ ሀገር ተምረው በመጡት ኢዮጵያውያን ላይ ተሰንዝሮ ለነበረው «የጥር ጣሬ ሐተታ» መልስ እንዲሆን ነበር ። ጽሑፍም ይህ ነው ፦—

"...አባቶቻቸውን ብዙ ኪሳራ አስከፍለው አውሮፓ ድረስ የሄዱ ልጆች ከትርጁማንነት በተቀር ሌላ ምን ይዘው ተምረው መጡ ። ትርጁማንነት ተምረው የመጡት ምናልባት ሀገራችንን ፈረንጆች የገዙት እንደሆነ እኛን ደንቆሮቹን ሊያስተረጁሙልን ይሆንን? አይሆንም...» የሚል የጥርጥር ሐተታ ፳፯ ኅዳር ፲፱፻፲፯ አእምሮ ቁጥር ፳፯ ላይ አንብበን እናዝናለን ።"

«የኢትዮጵያ ልጆች የሚበዙት እስካሁን ድረስ የአውሮጳ ቋንቋ የተቻላቸውን ያህል አውቀው ኢትዮጵያውያንና አውሮጳውያንን እያነጋገሩ ወይም ጽሕፈታቸውን ካንዱ ቋንቋ ወዳንዱ ቋንቋ እየተረጐሙ መንግሥትና ሕዝብን ለማገልገል

የበቁት በገዛ መልካም ፈቃዳቸው ብርታትና በአውሮጳው ያን እርዳታ እንደሆነ እንጅ በዘመዶቻቸው ኪሳራ እንዳ ልሆነ አስተዋይ የሆነ ሰው ሁሉ ያውቃል ።»

«ሠልጥነው የሚያስለጥኑ ሕዝቦች ቋንቋ መማራቸውም ለቀረው ትምህርት ሁሉ ዋና መክፈቻው አፍ ነውና በዚሁ አድርገን ጥበባቸውን ተምረን ስናበቃ ሀገራችንና መንግሥታችንን እያገለገልን እንደነሱ ልክ ነጻነትና ጥቅም ክብር ከወንድሞቻችን ጋር እናገኛለን ብለው ነው እንጅ ከላይ እንደተባለው የጥርጥር ሐተታ ባለቤት ሐሳብ የራሱ ብቻ ሳይሆን የሕዝቡም አገልጋይ አድርጐ ለሚገዛ ባዕድ መንግሥት ትርጁማኖች እየሆኑ የሰው ቋንቋ ከማያውቁት ወንድሞቻችን በላይ እናድራለን ብለው አይደለም…»

«የዚህ ሐተታ ባለቤት «መዠመሪ የአውሮጳ ብልሃት የጅ ሆነ የልብ ጥበብ ሁሉ ባማርኛ ተገልብጦ ልጆቻችን ቢማሩት መቸም ቋንቋቸው ነውና በፍጥነት ይገባቸዋል» ይላሉ ። እዚህ ላይ ይልቅ የሚያስፈልግ ነገር ተናግረዋል ። ነገር ግን የአውሮጳ ቋንቋ ያወቁ ኢትዮጵያውያንን ከጠረጠረና ከጠላ ይህ ደግ ሐሳቡ በማን ሊገለበጥ ያስበዋል»

«የኢትዮጵያ ልጆች ቋንቋ ብቻ እየተማሩ ወደ ሀገራቸው ለመመለሳቸውም ቀድሞ እንዳልነው በዘመዶቻቸው ከሳራ ሳይሆን በገዛ ፈቃዳቸው ብርታትና በፈረንጆች እርዳታ ነበርና ከቋንቋ ትምህርት ቤት ገብተው የነበሩት ወደ ጥበብና ዕውቀት ትምህርት ቀጽለን እንግባ ብለው ሲጣጣሩ ይህን ጊዜ የፈረንጆች እርዳታ የለምና የገንዘብ እጦት እንደ ክፉ አጋፋሪ ሆኖ ስለከለከላቸው ነው ።»

«(ስለዚህ መተባበርና የአውሮጳን ሥልጣኔ ማስገባት ነው እንጅ) «ምናልባት ፈረንጆች ሀገራችንን የገዟት እንደ ሆን ሊያስተረጁሙልን ይሆንን» የሚሉት የሰነፍ ክፉ ትንቢት በጋዜጣ አውጥቶ ማስታወቅ አይገባም ።»